ኢትዮጵያ

በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና በገዥው ፓርቲ በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የተቀናጀ አመራር ኢትዮጵያ ከአሃዳዊ ወደ ፌዴራላዊ የመንግሥት ሥርዓት የምታደርገውን ሽግግር ቀጥላለች፡፡ የአገሪቱ ሕዝብ ብዛት 74 ሚሊዮን ያህል ነበር፡፡ በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የተካሄደውን ምርጫ ውጤት መንግሥት በነሐሴ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. ያፀደቀ ሲሆን፣ በዚሁም ምርጫ ኢህአዴግ ለሦስተኛ ተከታታይ ጊዜ ለአምስት ዓመት ወቅት በምርጫው አሸናፊ ሆኗል፡፡ በብዙ የምርጫ አካባቢዎች ያለአግባብ የተከናወኑ አሠራሮች መፈጸማቸው እና በመራጮች እና በታዛቢዎችም ላይ ጫና የተደረገ ቢሆንም፣ በመላ አገሪቱ የድምፅ አሰጣጡ በአጠቃላይ ተአማኒ እንደነበረ የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፋዊ ታዛቢዎች ዘግበዋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአመዛኙ በጐሣ ላይ ተመሥርተው የነበሩ ቢሆንም፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሰባስበው በመጠናከር ሂደት ቀጥለዋል፡፡ በአጠቃላይ ሲቪል ባለሥልጣኖች የፀጥታ ኃይሎችን በሚገባ የተቆጣጠሩ ቢሆንም፣ ከፀጥታ ኃይሎች ውስጥ አንዳንድ ክፍሎች ከመንግሥት ሥልጣን ውጭ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰዳቸው በአንዳንድ ሥፍራዎች ተከሰቷል፡፡

ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫውን ውጤት አንቀበልም በማለታቸው የተነሳ፣ ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ በህዳር ወር ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት) ለሰላማዊ ተቃውሞ ጥሪ ካደረገ በኋላ የተሰፋፉ ረብሻ እና በፖሊስ እና በጦሩ ክፍል ከመጠን በላይ በኃይል መጠቀም ተፈጽሟል፡፡ አንዳንድ መሻሻሎች ቢታዩም፣ መንግሥት በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ያለው ሬኮርድ ዝቅተኛ እንደሆነ ከመቀጠሉም ባሻገር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በይበልጥ ብሶበታል፡፡ እስከ ግንቦቱ ብሔራዊ ምርጫ በነበረው ጊዜ ውስጥ፣ የምርጫ ውድድሩ ግልጽ ነበር፣ ክርክሮችም በቴሌቪዥን ተሰራጭተዋል፡፡ የካርተር ማዕከል ይህንን ወቅት ተአማኒነት የነበረው እና የሚመሰገን ነበር በማለት ገልጾታል፡፡ ሆኖም ግን፣ ከምርጫዎቹ ቀጥሎ በነበረው ወቅት ባለሥልጣኖች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን፣ የአናሳ ጐሣዎች ወገኖችን፣ የመያድ ሠራተኞችን፣ ጋዜጠኞችን ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ አግተዋል፣ ደብድበዋል፣ ገድለዋልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባለሥልጣኖች፣ የኘሬስ ነፃነትን፣ የመሰብሰብ ነፃነትን ጨምሮ፣ በሲቪል ነፃነቶች ላይ ተጨማሪ ማእቀብ ጭነዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት የሰብዓዊ መብቶች ችግሮች ተዘግበዋል፡-

- ዜጐች መንግሥታቸውን ለመለወጥ ያላቸው መብት መገደብ

- የፖለቲካ ግድያዎች የተባሉትን ጨምሮ፣ ሕገወጥ ግድያዎች፣ በታጋቾች እና በተቃዋሚዎች ደጋፊዎች ላይ የፀጥታ ኃይሎች ድብደባ፣ ማዋረድ እና ማንገላታትን መፈጸም
- ከሚገባው በታች የዘቀጡ የእሥር ቤት ሁኔታዎች
- በተለይ የተቃዋሚ ወገነተኞች ወይም አባላት ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩትን በሺሕዎች የሚቆጠሩትን ሰዎች በዘፈቀደ መያዝ እና ማገት፣ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ክስ ሳይመሠረትባቸው ማገት እና ዳኝነት ከመጀመሩ በፊት ለረጅም ጊዜ ማሰር
- የመንግሥት የዜጐችን ግላዊ መብቶች መፃረር እና የብርበራ ትዕዛዞችን በሚመለከት ያሉትን ሕጐች ለመከተል መንግሥት በተደጋጋሚ ያሳየው እምቢተኛነት
- የመንግሥት የኘሬስ ነፃነትን መገደብ፣ ጋዜጠኞች መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎችን በማሳተማቸው ይዞ ማሰር፣ ማገት እና ማዋከብ፣ በዚህም ምክንያት የጋዜጠኞች በእራሳቸው ላይ ማዕቀብ መጣል
- ፈቃድ መከልከል፣ ከባድ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ወይም ለተቃዋሚ የፖሊቲካ ስብሰባዎች የስብሰባ አዳራሾችን በመንፈግ፣ እና አንዳንድ ጊዜም ሰላማዊ ሰልፈኞችን ለመበተን ከመጠን ያለፈ ኃይል መጠቀምን ጨምሮ፣ የመንግሥት የመሰብሰብ ነፃነትን መገደብ
- የመንግሥት ማኅበር የመመሥረትን ነፃነት መገደብ
- በሴቶች ላይ በኃይል መጠቀም እና ማኅበራዊ ማግለልን መፈጸም፣ እና ሕፃናትን መድፈር
- ሴት ልጆችን መግረዝ
- ለኢኮኖሚ እና ግብረ ሥጋ ግንኙነት ዓላማዎች ሕፃናትን መበዝበዝ
- በሰዎች መነገድ
- አካላዊ ችግር/ጉድለት ባለባቸው ሰዎች ላይ፣ እንደዚሁም በሃይማኖት እና በጐሣ አናሳ በሆኑት ወገኖች ላይ የሚፈጸም ማኅበራዊ መድልዎ/ማግለል
- በማኅበራት እንቅስቃሴዎች ላይ የመንግሥት ጣልቃ መግባት

ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር

ክፍል 1 የሰውን ምሉእነት ማክበር፤ ይህም የሚከተሉትን ነፃነቶች ይጨምራል

ሀ/ በዘፈቀደ ወይም ሕገወጥ በሆነ አፈጻጸም ሕይወትን ከማጣት

በዓመቱ ውስጥ ወታደር ቀመስ ቡድኖች (ፓራሚሊታሪ ግሩፕስ) ፖለቲካዊ ግድያን ጨምሮ፤ ሕገወጥ ግድያዎች ፈጽመዋል። ከጥር እስከ መጋቢት ድረስ የታጠቁ ሚሊሺያዎች የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ የቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ (መኢአፓ/ቅአዲ) በርካታ አባላትን በአማራ ክልል መግደላቸውን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ዘግቧል። ለምሳሌ፤ ጥር 11 ቀን 1997 ዓ.ም. አንለይ አዲስ የተባለውን የመኢአፓ አባል እና እይልኝ ወንድሜነህ የሚባል የዚሁ ፓርቲ የአካባቢው ሊቀመንበር የነበረውን ሚሊሺያ ገድሏቸዋል። ሁለቱም ሰዎች የባባት ቀበሌ የደባይ ጥላትግን ወረዳ ነዋሪዎች ነበሩ። የካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም. በአንካሻ ወረዳ የሦስቱ ሹመታ ዘግሳ ቀበሌ ነዋሪ የነበረውን ጥላሁን ቀረበን፤ እና መጋቢት 12 ቀን ደግሞ በሺኮዳድ ወረዳ የአብሰላ ቀበሌ ነዋሪ የነበረውን አላምር አዕምሮን ሚሊሺያ ገድሏቸዋል። በዓመቱ መጨረሻ ላይ በጥላሁን ቀረበ ግድያ ሁለት ተጠርጣሪዎችን ፖሊስ ይዟል።

ከመጋቢት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. እስከ መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ ፖሊስ፤ ሚሊሺያ እና የቀበሌ አስተዳዳር ሹማምንት 24 አባላቱን እና ደጋፊዎቹን የጦር መሣሪያ ተኩሰው መግደላቸውን የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ) ዘግቧል። ለምሳሌ፤ መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. በኢጃኢ ከተማ ጨሊያ ወረዳ ነዋሪ የነበረውን አህመድ አደምን ፖሊስ የጦር መሣሪያ ተኩሶ ገድሎታል። በሰኔ 5 ቀን 1997 ዓ.ም. ፖሊስ መሣሪያ በመተኮስ በምሥራቅ ሸዋ የአርሲ ነገሌን ከተማ ወክሎ የፓርላማ ተመራጭ የነበረውን ተስፋዬ አዳነን ገድሎታል። ከእነዚህ ግድያዎች በአንዳንዶቹ ሁለቱም ወገኖች መሣሪያ ታጥቀው ከመፋጠጥ የተፈጠሩ ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ላይ በፓርላማ ተመራጩ በተስፋዬ አዳነ ግድያ የተጠረጠሩ ሦስት ፖሊሶች በዝዋይ ወህኒ ቤት ታስረው ምርመራው እንደቀጠለ ነበር። ሚያዝያ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የቀበሌ ሹማምንት በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፤ ወረይሉ ወረዳ፤ ቀበሌ 11 የቅንጅት አስተባባሪ የነበረውን ሀሰን እንድሪስን የቀበሌ ሹማምንት መሣሪያ ተኩሰው መግደላቸውን ኢሰመጉ ዘግቧል። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መሣሪያ ተኩሰው በኦሮሞ ክልል፤ ሻሸመኔ ወረዳ፤ የሁርሶ ሴምቦ ቀበሌ ነዋሪ የነበሩትን ሼክ ኦስማን ሃጂ አብደላን ገድለዋል።

በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በግቤ ወረዳ ነዋሪ የነበረውን በዘላ ላምቢሶን የምድር ጦር ሠራዊት ወታደሮች ነሐሴ 12 ቀን 1997 ዓ.ም. ገድለው ሚስቱን አስገድደው መድፈራቸውን የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፌዴራሊስት ፓርቲ (ኦሶዴፌፓ) ዘግቧል። በዘላ በ1992 ዓ.ም. ብሔራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎች በተደረጉበት ወቅት፣ አንድ ፖሊስ ገድሏል ተብሎ ክስ ሊመሠረትበት ነበር።

የቅንጅት ፓርቲ አባል የነበረው አሰፋ ጌታሁን መስከረም 1 ቀን 1998 ዓ.ም. በታጣቂ ሚሊሺያ ተደብድቦ በደረሰበት ጉዳት በማግሥቱ መሞቱን ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ዘግቧል። በሱሉልታ ወረዳ ሙሎ ከተማ ነዋሪ እና የቅንጅት አባል የነበረውን ግርማ ብሩን የአካባቢው ሚሊሺያ መስከረም 21 ቀን 1998 ዓ.ም. መሣሪያ ተኩሶ ገድሎታል። በአማራ ክልል፣ ምዕራብ ጐጃም/ጂጋ፣ ሾጋ ወረዳ በሞሴ ዋሴ ላይ ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ለተፈጸመው ሕገወጥ ግድያ፣ እና እንደዚሁም በሰሜን ጐንደር፣ ላይ ጋይንት/ነፋስ መውጫ ጥቅምት 6 ቀን 1998 ዓ.ም. በጥላ ፀጋ ላይ ለተፈጸመው ሕገወጥ ግድያ ሃላፊዎቹ የየሥፍራው አስተዳዳሪዎች እና የታጠቁ ሚሊሻዎች መሆናቸውን ቅንጅት አስታውቋል።

በጥቅምት 1997 ዓ.ም. በፖሊስ ተፈጽመዋል የተባሉትን በርካታ ገድያዎች ኢሰመጉ ዘግቧል። ለምሳሌ፣ ጥቅምት 8 ቀን በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ፣ በቀያ ገብርኤል ቀበሌ ነዋሪ የነበረውን ገለታው ማሞን ፖሊስ መሣሪያ ተኩሶ ገድሎታል። በግድያው የተጠረጠረ አንድ ሰው በጅማ ከተማ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውሏል። በቦሌ ክፍለ ከተማ፣ አዲስ አበባ፣ ዳቦ ጋጋሪ የነበረውን ነስረዲን ሸሼሎን በህዳር ወር 1996 ፖሊስ መሣሪያ ተኩሶ ገድሎታል። በግድያው ተጠርጥሮ የተያዘውን አንድ ግለሰብ ባለሥልጣኖች በዋስ ፈትተውታል። በኢሉ ወረዳ፣ ተጂ ከተማ ነዋሪ የነበረው አሸናፊ ታቦር በህዳር ወር 1996 ዓ.ም. በፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ተገድሏል። በግድያው የተጠረጠሩ ሦስት ሰዎች ሰበታ ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል። በታህሣሥ ወር 1996 ዓ.ም. በቂርቆስ ክፍል ከተማ፣ አዲስ አበባ በፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ለተገደለው ኤፍሬም ዓለማየሁ አንድ ተጠርጣሪ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ነበር። በሱማሌ ክልል፣ ጂጅጋ ከተማ በፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ለተገደለው ከበደ ዑዞ አንድ ተጠርጣሪ በጂጅጋ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ነበር።

በ1996 ዓ.ም. ውስጥ በፀጥታ ኃይሎች የተገደሉትን ሰዎች ጉዳይ በሚመለከት ምንም ያህል አዲስ የፍርድ ሂደት አልታየም። በመጋቢት ወር በኦሮሚያ ክልል የተገደለው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ዓለሙ ተስፋዬ፣ በኦሮሚያ ክልል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የነበረችው የዓመለወርቅ ቡሊ ግድያ፣ ከመጋቢት እስከ ግንቦት በመላ ኢትዮጵያ

አንድነት ፓርቲ (መኢአፓ) ደጋፊዎች ላይ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ በሰኔ ወር በጐዳ ከተማ የአንድ ወታደራዊ ሠራዊት ተሽከርካሪ ከሲቪል ተሽከርካሪ ጋር መጋጨት እና ታጣቂዎቹ ተኩስ ከፍተው 10 ሰዎችን መግደል፡፡

ኤሊሶ ቴሊሶ የተባለውን የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት አባል የነበረውን በ1995 ዓ.ም. ስለገደለው የወረዳ ፖሊስ ጉዳይ ምንም ለውጥ አልነበረም፡፡

ከግንቦት 1994 እስከ ታህሣሥ 1995 በጋምቤላ ክልል ከሕግ ውጭ በተገደሉት 13 የአኙዋክ ተወላጆች ወንጀል የተጠረጠሩት በርካታ ግለሰቦች ላይ የተመሠረተው ክስ ሂደት መጀመሩን መንግሥት ዘግቧል፡፡ የመንግሥት ወታደሮች በጋምቤላ ክልል በመቶዎች የሚቆጠሩ አኙዋኮችን መግደላቸውን፣ አስገድደው መድፈራቸውን እና ማሰቃየታቸውን አምኔሲቲ ኢንተርናሽናል በመጋቢት 1997 ዓ.ም. ዘግቧል፡፡

ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 1 ቀን በነበረው ጊዜ ውስጥ ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት በአዲስ አበባ ውስጥ ባልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ተኩስ ከፍተው 42 ሰዎች መግደላቸውን ኢሰመጉ በ1997 ዓ.ም. ዘግቧል፡፡ ከጥቅምት 22 እስከ 28 ቀን 1998 ዓ.ም. የመከላከያ ሠራዊት እና የፖሊስ ኃይሎች ድንጋይ ሲወረውሩ በነበሩ ረባሾች፣ አንዳንዶቹም ቆንጨራ እና የእጅ ቦምብ ይዘው በነበሩት ላይ ተኩስ ከፍተው ቢያንስ 40 የሚሆኑ ሰዎችን በአዲስ አበባ ውስጥ ገድለዋል (ክፍል 2ለን ይመልከቱ)፡፡ ለምሳሌ፣ ግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተፈጠረውን ማንገራገር ተከትሎ የየካ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የነበረውን ሽብሬ ደሳለኝን እና በኮተቤ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ተማሪ የነበረውን የሱፍ አብደላን ፖሊስ መሣሪያ ተኩሶ ገድሏቸዋል፡፡ ሰኔ 1 ቀን ደግሞ የኮልፌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ሆኖ ዕድሜው 16 ዓመት የነበረውን ተማሪ ነቢይ ዓለማየሁን፣ እና የሰባት ልጆች እናት የሆነችውን ዙሉፋ ሱሩርን ፖሊስ በጥይት ገድሏቸዋል፡፡ የፀጥታ ኃይሎች ደግሞ ዕድሜያቸው 16 ዓመት የነበረውን ፈቃዱ ነጋሽ እና አብርሃም ይልማ የተባሉ ሁለት ወንድማማቾችን ገድለዋል፡፡ ሕገ ወጥ ሰልፍን ተከትሎ 26 ሰዎች መሞታቸውን ፌዴራል ፖሊስ አስታውቋል፡፡ በህዳር ወር ውስጥ በተፈጠረው ረብሻ በርካታ ፖሊሶችም ተገድለዋል፡፡ የግድያዎቹን ሁኔታ እንዲያጣራ ህዳር 28 ቀን መንግሥት አንድ ነፃ ኮሚሽን አቋቁሟል፡፡ ኮሚሽኑም መረጃ እና አቤቱታዎች እንዲቀርቡለት በይፋ ጠይቋል፡፡

በሐምሌ 17 እና 19 ቀን ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች በጅጅጋ 4 ሆቴሎች ውስጥ እና በአንድ መኖሪያ ቤት ላይ የእጅ ቦምቦች አፈንድተው 5 ሰዎችን መግደላቸውንና

በ31 ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ኢሰመጉ ዘግቧል፡፡ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ይዞ ጉዳዩ በምርመራ ላይ ይገኛል፡፡

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) እና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) ታጣቂ ቡድኖች በአገሪቱ ውስጥ እንቅስቃሴያቸውን ቀጥለዋል፡፡ ለበርካታ ጊዜያት ከመንግሥት ኃይሎች ጋር ያካሄዷቸው የተኩስ ልውውጦች በሰላማዊው ሕዝብ፣ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች፣ በኦነግ እና ኦብነግ ወታደሮች እንዲሁም አባላት ላይ በቁጥር ያልታወቀ ሞት አስከትሏል፡፡

በዓመቱ ውስጥ ሁለት ሚሊዮን ያህል በመሬት ውስጥ የተቀበሩ ፈንጅዎች በአገሪቱ ውስጥ ነበሩ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከ1990–1992 ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት ቅሪት የሆኑ ብዙ ነበሩ፡፡ በዓመቱ ውስጥ በመሬት የተቀበሩ ፈንጅዎች ከኤርትራ ጋር በሚዋሰኑ ወረዳዎች ሰባት ሰላማዊ ሰዎችን ገድለዋል፣ በአስር ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ ሰባት ተሽከርካሪዎችን አውድመዋል፡፡ የመንግሥት ፈንጅ አምካኝ ቡድን በወሰን አካባቢዎች የተቀበሩ ፈንጅዎችን በመቃኘት እና በማምከን ረገድ በተወሰነ ደረጃ ገፍቶበታል፡፡ በዓመቱ ውስጥ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ ድንበር በሁለቱም በኩል አዲስ ፈንጅዎች መቀበራቸውን በኤርትራ እና በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ልኡካን ቡድን (ሚሺን) ባለሥልጣኖች ዘግበዋል፡፡ በተመረጡ የወሰኑ አካባቢዎች መንግሥት እና ሚሽኑ የማምከን ሥራዎችን ከመፈጸማቸውም ባሻገር፣ ፈንጅ ተቀብሮባቸዋል ተብሎ ስለሚጠረጠሩ አካባቢዎች ለሥፍራው ነዋሪዎች መረጃዎችን አሰራጭተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (አአዩ) የቴሌቪዥን መመልከቻ ክፍል ውስጥ የትግርኛ ቋንቋ የዜና ፕሮግራም በሚሰራጭበት ወቅት በሚያዝያ ወር 1996 ዓ.ም. በተወረወረው የእጅ ቦምብ ተጠርጥረው የታሠሩ ሰዎች በሰኔና ሐምሌ ወራት 1997 ዓ.ም፣ በጥቅምት እና ህዳር 1998 ዓ.ም. ፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ ጉዳዩ ለጥር 1998 ዓ.ም. ተቀጥሮ ነበር፡፡

በኦሮሚያ ክልል፣ ደብረ ዘይት ከተማ ባለቤቱ የትግራይ ተወላጅ በሆነ ሱቅ ላይ በ1996 ዓ.ም. የተጣለውን የእጅ ቦምብ በሚመለከት የተገኙ ለውጦች አልነበሩም፡፡ ፖሊስ አደጋውን ያደረሰው ኦነግ ነው ብሏል፡፡

በዓመቱ ውስጥ በተቀሰቀሱ የጐሣ ግጭቶች ምክንያት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል (ክፍል 5 ይመልከቱ)፡፡

ከ1966 እስከ 1983 ዓ.ም. በቆየው የደርግ አገዛዝ ወቅት ከሕግ ውጭ መግደልን ጨምሮ የዘር ማጥፋትና ሌሎችንም የጦርነት ወንጀሎችን ፈጽመዋል ተብለው በይፋ በተከሰሱት ላይ በአዲስ አበባ የሚያስችለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መስማቱን እና ፍርድ/ብይን መስጠቱን ቀጥሏል (ክፍል 1ሠ ይመልከቱ)

ለ/ መሰወር

በዓመቱ ውስጥ በመንግሥት ኃይሎች የተፈጸሙ ሰዎችን የመሰወር ድርጊቶች እንደነበሩ ዘገባዎች አመልክተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ ፖሊቲካዊ መንስዔ ሳይኖራቸው እንዳልቀረ ይገመታል፡፡ ከሞላ ጐደል በሁሉም ሁኔታዎች የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሰዎችን አፍነው በመውሰድ የት እንደሆኑ ባልተገለፀ ሥፍራዎች ከሳምንታት እስከ ወራት ለተራዘመ የተለያየ ወቅት አግተዋቸዋል፡፡ በኦሮሚያ ውስጥ በመንግሥት ላይ ትግል እንዲካሄድ ኦነግ ላደረገው ጥሪ የተሰጠውን ምላሽ ተከትሎ እና ከምርጫው በኋላ በህዳር እና ታህሣሥ ወራት ሰላማዊ ሰልፎች በተደረጉበት ወቅት እነዚህን የመሰሉ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ድርጊቶች ተፈጽመዋል፡፡

በሰኔ 1 እና 3 ቀን 1997 ዓ.ም. መካከል 17 ሰዎች እንደተሰወሩ (የደረሱበት እንዳልታወቀ) ኢሰመጉ ዘግቧል፡፡ ሰኔ 1 ቀን አዲስ አበባ ውስጥ አሸናፊ ብርሃኑን፣ ፀጋዬ ንጉሴን፣ ዳንኤል ወርቁን እና አደም ሁሴንን ሁሉንም ከሥራ ገበታቸው ላይ፤ በአዲስ አበባ ውስጥ በአራዳ ክፍለ ከተማ ይኖር የነበረውን ጀላሉ ተማምን፣ በልደታ ክፍለ ከተማ ይኖሩ የነበሩትን ግሩም ሠይፉን እና መኮንን ሠይፉ የተባሉትን ሁለት ወንድማማቾች ፖሊስ አፍኖ ወስዷቸዋል፡፡ ሰኔ 2 ቀን ደግሞ የፀጥታ ኃይሎች በአዲስ አበባ ውስጥ፣ ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ እንደሻው ተረፈን አፍነው ሲወስዱ፣ ፌዴራል ፖሊስ በበኩሉ ዳንኤል አበራን፣ ተስፋዬ ባቻን፣ ተስፋዬ ጀመናን፣ ቦንሳ በየነን እና ጌቱ በዟን ከአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ አፍኖ ወስዷል፡፡ እንደዚሁም ሰኔ 3 ቀን መኖሪያቸው ወረዳ 9 ቀበሌ 7 የሆነው ሰሎሞን በቀለ ከልደታ ክፍለ ከተማ እና አማኑኤል አሥራት፣ መስፍን መርጊያ እና ዳዊት ደመረው በፌዴራል ፖሊስ ታፍነው ተወስደዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ግለሰቦች የት እንደሚገኙ አይታወቅም ነበር፡፡

መንግሥታዊ ያልሆነው የኦሮሞ ድርጅት (መያድ) የሜጫ እና ቱሉማ ማኅበር የጥበቃ ሠራተኛ/ዘበኛ የነበረው እና በ1996 ዓ.ም. የታገተውን ጅግሣ ሶሬሳን ምንም አዲስ ነገር ያልነበረ ሲሆን፣ እንደተዘገበው ከሆነ ግለሰቡ በአዲስ አበባ ወህኒ (ማረሚያ) ቤት እንደታሠረ ነው፡፡

በ1996 ዓ.ም. ተሰውሮ የነበረው ኦሮሞው ዘፋኝ ራያ አባሜጫ አዲስ አበባ መመለሱን መንግሥት እና ነፃ ምንጮች ዘግበዋል፡ በዓመቱ መጨረሻ የራያ መሰወር ዝርዝር ሁኔታ አልታወቀም ነበር፡፡

ሦስት የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሠራተኞች ሰኔ 2 ቀን አንድ ወታደራዊ ሄሊኮፕተር በአምቡሊ ጂቡቲ፣ አሳርፈው፣ ሁለቱ ጥገኝነት መጠየቃቸው የተዘገበ ቢሆንም፣ አንድ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ልዑካን ቡድን ወደ ሥፍራው ሄዶ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ አሳምኖአቸው በማግሥቱ መመለሳቸው ተዘግቧል፡፡ ዓለም አቀፋዊ የጥገኝነት ድርጅት እና የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ተጠሪዎች ተጠቃሾቹን በጅቡቲ ለመጐብኘት ሞክረው ተከልክለዋል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ አብራሪዎቹ በአንድ አየር ኃይል ሰፈር ታሥረው እንደሚገኙ እና ጐብኝዎችን ማየት የተከለከሉ መሆኑን የቤተሰቦቻቸው አባላት ለአገር ውስጥ ኘሬስ ገልጸዋል፡፡

ሐ/ ማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢሰብዓዊ ወይም አዋራጅ አያያዝ ወይም ቅጣት

ሕጉ በማሰቃየት እና በማንገላታት መጠቀምን የሚከለክል ቢሆንም፣ የፀጥታ ሹማምንት ብዙ ጊዜ ታጋቾችን እንደሚደበድቡ ወይም እንደሚያንገላቱ የሚገልጹ ብዙ ዘገባዎች አሉ፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊስ እና የክልል ሚሊሺያዎች አዘውትረው እና በታቀደ ሁኔታ ደጋፊዎቻቸውን እንደሚያንገላቱ እና እንደሚያዋርዱ ዘግበዋል፡፡

አብደታ ዲታ እንተሌ የሚባል የተቃዋሚው የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ/የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጎብረት አባል እና በኦሮሚያ ክልል የሲራሮ ወረዳ ነዋሪ የነበረ፣ በቀበሌ ሹማምንት ከባድ ድብደባ ከተፈጸመበት በኋላ በገዛ እራሱ ሕይወቱን ማሳለፉን ኢሠመጉ ግንቦት 6 ቀን ዘግቧል፡፡

ሽጉጥ የያዙ ሁለት ሰዎች ጥቅምት 6 ቀን 1998 ዓ.ም፣ ዳንኤል በቀለ የተባለውን አክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ለተሰኘው መያድ የፖሊሲ ሃላፊ እና የግንቦት 7ን ምርጫዎች የተከታተለው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መረብ እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የነበረውን ደብድበውታል፡፡ አክሽን ኤይድ እንደገለጸው ታጣቂዎቹ ዳንኤል በቀለን ዓይኑ ላይ መትተውታል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ዳንኤል በቀለ በአገር ክህደት እና በዘር ማጥፋት ወንጀሎች ተከስሶ በፖሊስ እንደታሰረ ነበር፡፡

በየካቲት እና መጋቢት ወራት 1996 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች ፖሊስ በተማሪዎች፣ መምህራን እና ወላጆች ላይ የፈጸመውን ድብደባ በሚመለከት፣ ወይም ሚሊሺያ በተቃዋሚው የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አባላት ላይ የፈጸመውን ማጥቃት እና ፓርቲው ለሚመለከታቸው ያሳወቀውን በሚመለከት ባለሥልጣኖች በአጥፊዎቹ ላይ ምንም እርምጃ አልወሰዱም። ሰላማዊ ሰልፎች በሚደረጉበት ወቅት የፀጥታ ኃይሎች ሰዎችን ደብድበዋል (ክፍል 2.ለን ይመልከቱ)።

ቁጥራቸው ያልተገለጸ፣ ነገር ግን ወደ 330 የሚሆኑ ተማሪዎች በጥቅምት 1997 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተባርረዋል። ይኸም የተደረገው ቀደም ብሎ በጥር 1996 ዓ.ም. ኦሮሞ ተማሪዎች በሹል ኮረት ላይ ለረጅም ሰዓታት በባዶ እግራቸው እንዲንበረከኩ እና እንዲሮጡ በፖሊስ መታዘዛቸውን ተማሪዎቹ ስለተቃወሙ ነው። የተባረሩት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲው እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸዋል (ክፍል 2.ለ ይመለከቱ)።

በ1995 ዓ.ም. በፀጥታ ኃይሎች የተፈጸሙትን ድብደባዎች እና ማሰቃየት በተመለከተ ምንም ያህል ለውጦች አልነበሩም።

ቀደም ሲል ከነበሩት ዓመታት በተለየ ሁኔታ የፀጥታ ኃይሎች ጋዜጠኞችን ስለመደብደባቸው ዘገባዎች አልነበሩም።

ነሐሴ 5 ቀን የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፋዊ የዜና ማሰራጫዎች የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀድሞው የመንግሥት አገዛዝ ወቅት የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን አሰቃይተዋል ተብለው የተከሰሱትን ከፍተኛ የቀድሞው መንግሥት ሹማምንት፣ የቀድሞውን የሀገርና የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስትር ተስፋዬ ወልደ ሥላሴን እና የቀድሞ የወንጀል ምርመራ ሃላፊ ለገሠ በላይነህን በሞት እንዲቀጡ የፈረደባቸው መሆኑን ዘግበዋል።

በዓመቱ ውስጥ የገሥግ ግጭቶች በመቶዎች የሚቆጠሩ የአካል ጉዳቶችን እና ሞት አስከትለዋል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)።

ወህኒ ቤቶችና የማገቻ ማዕከሎች ሁኔታ

የወህኒ ቤቶች እና እስረኞች ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት ተይዘው የሚቆዩባቸው ማዕከሎች ሁኔታ በጣም አስከፊ እንደሆነ ነበር፣ መተፋፈግም ከፍተኛ ችግር እንደሆነ

ቀጥሏል፡፡ እስከ 200 የሚሆኑ አስረኞችን ሊይዝ በሚችል አንድ ክፍል ውስጥ፣ ብዙውን ጊዜ ለአስረኞች በነፍስ ወከፍ የሚፈቀድላቸው የመኝታ ሥፍራ ከ21.5 ካሬ ፊት (1.99735) ካሬ ሜትር ያነሰ ነበር፡፡ ለእያንዳንዱ እሥረኛ የዕለት ምግብ በጀቱ 25 የአሜሪካ ሳንቲም ወይም 2 ብር በመሆኑ፣ ብዙ እስረኞች ቤተሰቦቻቸው በየቀኑ ምግብ እንዲያቀርቡላቸው ያደርጋሉ ወይም በገዛ ገንዘባቸው ከአካባቢው ነጋዴዎች ምግብ ይገዙ ነበር፡፡ እስር ቤቶቹ ንጽህና የጐደላቸው፣ የሕክምና አገልግሎቶቹም የማያስተማምኑ ነበሩ፡፡ ለእስር ቤት ጥገና በጀት አልነበረም፡፡

በማገቻ ማዕከሎች ፖሊስ ብዙውን ጊዜ ታገቾችን ይደበድባል፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኦሮሚያ ውስጥ የታገቱ ተማሪዎች የተፈጸሙባቸውን ድብደባዎች በቅርብ ያወቁ/የተመለከቱ ዲኘሎማቲክ ታዛቢዎች ይህን ሁኔታ ዘግበዋል፡፡

አኃዛዊ መረጃዎች/ስታቲስቲኮች ባይገኙም፣ በእስር ቤቶች ውስጥ በህመም እና በጤና እንክብካቤ ዝቅተኛነት የተነሳ አንዳንድ እስረኞች ሞተዋል፡፡ የእስር ቤት ሹማምንት እነዚህን የመሳሰሉ የሞት ዘገባዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡

ባለሥልጣኖቹ አንዳንድ ጊዜ በጠባይ ማረሚያ ሥፍራ ያልተገኘላቸውን አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች፣ ከጐልማሶች ጋር አስረዋል፡፡ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆነ ልጆች ታስቦ የተሠራ 150 ልጆችን የሚይዝ አንድ የጠባይ ማረሚያ እና ማረፊያ ቤት ብቻ ነበር፡፡

በህዳር ወር በአዲስ አበባ ውስጥ ቤት ለቤት በተደረገ ሰፊ አሰሳ ወቅት መንግሥት ከ10 እስከ 18 ሺህ የሚደርሱ ግለሰቦችን (በአብዛኛው ዕድሜያቸው 18-23 የሆነ ወጣቶችን) ከዋና ከተማው በ375 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ እሚገኘው እና በደርግ አገዛዝ ወቅት ወታደራዊ ማሰልጠኛ ወደነበረው ዶዴሣ ወታደራዊ ሰፈር ማጓጓዙን የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ዘግበዋል፡፡ የሰፈሩ እማይደረስበት ቦታ መሆን እና የአገልግሎቶች አለመኖር ለታጋቾቹ ጤንነት ጠንቅ እንደሚሆን ታዛቢዎች ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡ በባሕር ዳር አካባቢ በሚገኙት ተመሳሳይ የማገቻ ሰፈሮች ላይ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ዘግበዋል፡፡ ከእነዚህ ታጋቾች ውስጥ አብዛኞቹ በዓመቱ መጨረሻ ተፈትተዋል፡፡ በዚያው በህዳር ወር መንግሥት በአገሪቱ ውስጥ ወደ እሚገኙ ሌሎች የማገቻ ሥፍራዎች ቁጥራቸው ያልታወቀ ሌሎች ታጋቾችን አጓጉዟል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ መንግሥት ከሦስት ሺሕ በቀር የቀሩትን ታጋቾች በሙሉ መፍታቱን በይፋ አስታውቋል፡፡ ያልተፈቱት ደግሞ የበርካታ ወራት እስር ሊያስከትሉ በሚችሉ በአንዳራዊ መልኩ ጥቃቅን ወንጀሎች ክስ

እንደሚመሠረትባቸውም ተገልጿል፡፡ ዓለም አቀፋዊ ታዛቢዎች ማገቻ ቦታዎቹን ከመጐብኘት ቢከለከሉም፣ የእስር ቤቶች አገልግሎት ሕብረት በኢትዮጵያ የተባለው የአገር ውስጥ መያድ ጉብኝት ተፈቅዶለት ነበር፡፡

በዓመቱ ውስጥ የቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ ኮሚቴ (ICRC) በአጠቃላይ በአገሪቱ በሙሉ ወደ ፌዴራል እና የክልል አስር ቤቶች (ማረማያ ቤቶች)፣ የሲቪል ማገቻ ሥፍራዎች እና የፖሊስ ጣቢያዎች እንዲሄድ ተፈቅዶለት ሺሕዎች ታጋቾችን ያካተቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጉብኝቶችን አድርጓል፡፡ እንደዚሁም አስቀድመው ለማረሚያ ቤቶች ሹማምንት በማሳወቅ የዲኘሎማቲክ ሚሲዮኖችም መጐብኘት እንዲችሉ መንግሥት ፈቅዶ ነበር፡፡ ሦስተኛ ወገኖች ሳይኖሩ ቀይ መስቀል ዓለማቀፋዊ ኮሚቴ በመደበኛ መርሃ ግብር ከእስረኞች ጋር እንዲገናኝ ባለሥልጣኖች ፈቅደውለታል፡፡ መንግሥት በኦነግ ተዋጊነት የሚጠረጥራቸውን የሚያግትበትን ወታደራዊ ሰፈሮች ይኸው ድርጅት እንዲጐበኝ ተፈቅዶለታል፡፡ "ለብሔራዊ ደህንነት ሲባል ነው" በሚል የታገቱ የኤርትራ ተወላጆችን እና ተወላጅነታቸው የኤርትራ ሆኖ በኢትዮጵያ ዜግነት የሚኖሩትንም ኮሚቴው መጐብኘቱን ቀጥሏል፡፡

የጦር ወንጀለኞች እና ሽብርተኞች ናቸው በማለት የልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ያሳገታቸውን ከፍተኛ ታጋቾች ዲኘሎማቶች እንዲጐበኙ መንግሥት መፍቀዱን ቀጥሏል፡፡ ሆኖም ግን የቀይ መስቀል ዓለማቀፋዊ ኮሚቴን ጨምሮ የዓለምአቀፍ ማህበረሰብ አባላት፣ በአዲስ አበባ በተካሄደው ፀረ-መንግሥት ሰልፍ አሉበት ተብለው ካለፈው ህዳር ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 22 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ማዕከላዊ ምርመራ በፌዴራል ፖሊስ ታግተው የሚገኙትን የተቃዋሚው የቅንጅት ፓርቲ መሪዎችን፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ስብስቦች አባላትን እና ጋዜጠኞችን እንዳይገናኙ መንግሥት ከልክሏል፡፡ የእስር ቤቶች አገልግሎት ሕብረት በኢትዮጵያ እና የአገር ውስጥ የሃይማኖት መሪዎች እነዚህኑ ታጋቾች እንዲጐበኙ መንግሥት ፈቅዶላቸዋል፡፡

መ. ከሕግ ውጭ መያዝ ወይም ማገት

ሕጉ ከሕግ ወጭ መያዝን እና ማገትን የሚከለክል ቢሆንም፣ ብዙውን ጊዜ መንግሥት በአሠራሩ እነዚህን ድንጋጌዎች አያከብራቸውም፡፡

የፖሊስ እና የፀጥታ/የደህንነት ተቋም ሚና

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ነው፡፡ ሚኒስቴሩ በበኩሉ በፓርላማ ሥር ነው፡፡ የአካባቢ መንግሥት ሚሊሺያዎችም እንደአካባቢ

የፀጥታ ኃይሎች የተንቀሳቀሱ ሲሆን እነዚህም በአብዛኛው ከፖሊስ እና ከወታደራዊ ኃይል ነፃ ናቸው፡፡ በፖሊስ ኃይል ውስጥ ጥቃቅን የሙሰኝነት ችግር እንደቀጠለ ቆይቷል፡፡ በተለይም የትራፊክ ፖሊስ አባላት ከአሽከርካሪዎች ጉቦ ይጠይቁ ነበር፡፡ ማንአለብኝነትም ከባድ ችግር እንደሆነ ነው፡፡ እነዚህን ስለመሳሰሉ ጥፋቶች የሚደረጉትን ምርመራዎች ውጤቶች መንግሥት በአብዛኛው ለሕዝብ አልገለጸም፡፡ ፌደራል ፖሊስ ብዙዎቹ የእራሱ የፖሊስ ኃይል አባላት፣ እንደዚሁም የክልል ፖሊሶች ሙያተኛነት እንደሚጐድላቸው አምኗል፡፡

መንግሥት ምልምል ፖሊሶችን እና ወታደሮችን በሰብዓዊ መብቶች ለማሠልጠን ጥረቶቹን ቀጥሏል፡፡ ስለሰብዓዊ መብቶች የሚሰጠውን ሥልጠና ሙያዊ ለማድረግ እና ሥርዓተ ትምህርቱም ስለሰብዓዊ መብት ዓለምአቀፋዊ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች የበለጠ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ፣ መንግሥት የዓለም አቀፋዊ የቀይ መስቀል ማሕበር ኮሚቴን ዕርዳታ መፈለጉን ቀጥሏል፡፡

በሰኔ 1997 እና በህዳር የተካሄዱትን፣ ሁከት ያስከተሉ ሰልፎች ሁኔታ እንዲመረምር አባላቱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሾሙለትን ኮሚሽን ፓርላሜንት ባለፈው ህዳር አቋቁሟል፡፡ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር የፀጥታ ኃይሎች ካስፈለገው በላይ በኃይል ተጠቅመዋል የሚባለውን ከየካቲት 1998 ዓ.ም. ጀምሮ እንደሚመረምር ለአንድ የውጭ አገሮች/አምባሳደሮች ስብስብ ገልጸዋል፡፡

መያዝ እና ማገት

ባለሥልጣኖች ካለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ሰዎችን ይዘው ማገትን አዘውትረው የተጠቀሙ ሲሆን፣ በተለይ ራቅ ባሉ ክልሎች የእነዚህ እና በህዳር ረብሻ ወቅት የታፈሱት በሺህዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች፣ የሕግ አማካሪዎች እና ቤተሰብ አባላት ታጋቾቹን እንዳይገናኙ ከልክለዋል፡፡ በሕጉ መሠረት፣ ታጋቾች በ48 ሰዓት ውስጥ የሚመሠረትባቸው ክስ ሊነገራቸው ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ግን ይህ ድንጋጌ በአሠራር አይከበርም፣ በዋስ የመለቀቅ ሥርዓት ቢኖርም፣ ሰው መግደልን፣ የአገር ክህደትን፣ እና ሙሰኛነትን ጨምሮ ለአንዳንድ ጥፋቶች አይፈቀድም፡፡ ብዙውን ጊዜ ባለሥልጣኖች የዋስትናውን መጠን ከ1 ሺሕ እስከ 10 ሺሕ ብር የሚወሰኑ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ለአብዛኞቹ ዜጐች ከአቅም በላይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠርጣሪዎች በዋስ እንዲለቀቁ ፍርድ ቤት የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች የፖሊስ ሹማምንት ሁልጊዜ አያከብሩም፡፡ ፍርድ ቤት ሲፈቅድ፣ ፖሊስ ምርመራውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ

በከፍተኛ ጥፋት የተጠረጠሩ ሰዎች ለ14 ቀናት ይታገታሉ፡፡ ምርመራው እንዲቀጥልም ለተጨማሪ 14 ቀን ጊዜያት እዚያው በእገት ይቆያሉ፡፡ በይፋ ከታወቁ የማገቻ ማዕከሎች ውጭ ሰዎችን በሌላ ማናቸውም ሥፍራዎች ማገትን ሕጉ ይከለክላል፡፡ ሆኖም ግን በደርዘኖች የሚቆጠሩ እና በይፋ ያልታወቁ ቅጥ የሌላቸው የአካባቢ መንግሥት ሚሊሺያዎች የሚጠቀሙባቸው የማገቻ ማዕከሎች ነበሩ፡፡ በህዳር ረብሻ ወቅት እና ከዚያም በኋላ በኦሮሚያ ክልል አንድ የፖሊስ ማሠልጠኛ ሠፈርን እንደ ጊዜያዊ እስር ቤት ሲጠቀሙበት ነበር፡፡

የግል የሕግ አማካሪ እና ጠበቃ ማቆም ላልቻሉ ታጋቾች መንግሥት ጠበቃ አቁሞላቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሲደርስ ነው፡፡ የክስ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ባለው የእገታ ወቅት ግን ባለሥልጣኖች ታገቾች ከሕግ አማካሪ ጋር እንዲገናኙ ጨርሶ አይፈቅዱም፤ ከፈቀዱም ለአጭር ጊዜ ነው፡፡

በትናንሽ ከተሞች ሰዎችን ከዳኛ ጋር ሳይገናኙ ባለሥልጣኖች ለረጅም ጊዜያት በፖሊስ ጣቢያዎች እንደሚያግቱ፣ አንዳንድ ጊዜም ሰዎች ያሉበት ቦታ ሳይታወቅ ለብዙ ወራት እንደሚቆዩ ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ብዙ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ፖሊቲካዊ ስብሰባዎች በመሳተፋቸው፣ የመንግሥት ሚሊሺያዎች ደጋፊዎቻቸውን በመደብደብ ያገቷቸው ስለመሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙ አቤቱታዎችን አስመዝግበዋል (ክፍል 1.ሐ ይመልከቱ)፡፡

በተለይ በኦሮሚያ እና በትግራይ፣ መንግሥት መምህራንን ማዋከቡን ቀጥሎበታል፡፡ መንግሥት በጣም ብዙ መምህራንን አግቶ የኦነግ አፍቃሪዎች ናችሁ ብሎ እንደ ወነጀላቸው እና ብዙዎቹም እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ በእስር ቤት እንደነበሩ ነፃው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ) ዘግቧል፡፡ ከእነዚሁ መምህራን ውስጥ እንዳንዶቹ ክስ ሳይመሠረትባቸው ብዙ ዓመታት በእገታ ቆይተዋል፡፡ ለረጅም ጊዜያት የቀጠሉት እገታዎች ፖሊቲካዊ ምክንያት እንደሚኖራቸው የሰብዓዊ መብቶች ታዛቢዎች ጠርጥረዋል፡፡

ፖሊስ እንዳሻው ወደ የግል መኖሪያ ቤት መግባቱን እና ካለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ግለሰቦችን መያዙን ቀጥሏል፡፡

በዓመቱ ውስጥ ፖሊስ ጋዜጠኞችን አግቷል (ክፍል 2.ሀን ይመልከቱ)፡፡

በሚያዝያ እና ግንቦት ወራት 1996 ዓ.ም. የመኢአድ አባላትን ከሕግ ውጭ ባገቱት የአማራ ክልል የመንግሥት ሚሊሺያዎች፣ የወረዳ ሹማምንት፣ ፖሊስ ላይ፣ ወይም ከግንቦት እስከ ሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም. የኦብኮ አባል የሆነውን ኦልባና ሌሊሳን ክስ ሳይመሠርት ከሕግ ውጭ ባገተው ፖሊስ ላይ ባለሥልጣኖች ምንም እርምጃ አልወሰዱም፡፡

በዓመቱ ውስጥ ሰዎች ስብሰባ እና ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ፖሊስ አግቶአቸዋል (ክፍል 2.ለን ይመልከቱ)፡፡

በልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ትዕዛዝ ከታገቱት አንዳንዶቹ በፖሊቲካዊ ምክንያት ነው በማለት ተቃዋሚዎች ስሞታ አሰምተዋል፡፡ መንግሥት በበኩሉ ስሞታውን አስተባብሏል (ክፍል 1.ሠን ይመልከቱ)፡፡

የግንቦት 7 የፓርላሜንት ምርጫዎችን ውጤት አስመልክቶ የተሰጠውን መግለጫ በመቃወም ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 2 ቀን ትዕይንተ ሕዝብ ከተደረገ በኋላ ፖሊስ በሺህዎች የሚቆጠሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን እና ሌሎችንም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እያፈሰ አግቷል፡፡ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ከሦስት እስከ አራት ሺህ የሚደርሱ ነዋሪዎችን ከየቤታቸው ወስደው ከዋና ከተማው ራቅ ብሎ በሚገኝ የዝዋይ ወህኒ ቤት አግቷቸዋል፡፡

በሰኔ 3 እና 9 ቀን መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥ 74 የተቃወሚ ፖሊቲካ ፓርቲ አንቀሳቃሾች፣ ነጋዴዎች፣ እና ተማሪዎች ሕገወጥ በሆነ አኳኋን መታገታቸውን ኢሠመጉ ዘግቧል፡፡ የፀጥታ ኃይሎች በአምስት ሺህ የሚገመቱ ግለሰቦችን እየደበደቡ በመያዝ፣ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ እሥር ቤቶች አግተዋቸዋል፡፡ ሰኔ 22 ቀን ፌዴራል ፖሊስ 4,455 "ተጠርጣራዎችን" ማገቱን ዘግቧል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ከብዙ ቀናት እገታ በኋላ ተለቅቀዋል፡፡ ሆኖም፣ በመስከረም ወር አጋማሽ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን በሚገኘው በሸዋ ሮቢት ወህኒ ቤት ከነበሩት እስረኞች ውስጥ 40 ከመቶ (ከ1,866 እስረኞች ውስጥ 742) በሰኔ ወር በተካሄዱት ትዕየንተ ሕዝብ ወቅት በአደገኛ ቦዘኔነት የተከሰሱ ወንድ ወጣቶች ነበሩ፡፡

በመስከረም ወር መንግሥት ከአንድ ሺህ በላይ የሆኑ የቅንጅት እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ጥምር ተቃዋሚ አባላትን አሰሯል፡፡ ይህንንም ያደረገው በመስከረም 2 ቀን ትዕይንተ ሕዝብ ለማካሄድ ዕቅድ መያዛቸውን ካሳወቁ በኋላ ነው፡፡ በህዳር ወር ከ30 እስከ 200 የሚሆኑ አሽከርካሪዎች፣ ሰላማዊ

እምቢተኝነት እንዲካሄድ ተቃዋሚው ወገን ላደረገው ጥሪ ምላሽ በመስጠት፣ የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት በሚካሄድበት ዕለት የተሸከርካሪ ጥሩምባዎችን በማሰማታቸው ከሕግ ውጭ ታግተዋል፡፡

በህዳር ወር ውስጥ ወታደር ፖሊስ በአዲስ አበባ ብዙውን ጊዜ ሌሊት ከቤት ወደ ቤት ብርበራዎችን በማካሄድ ዕድሜያቸው በ18 እና በ23 ዓመት መካከል የሆነ ከ10 እስከ 18 ሺህ የሚሆኑ ወጣቶችን ፀረ-መንግሥት በሆነ የረብሻ ትዕይንተ ሕዝብ ተሳትፈዋል በሚል ካለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ አግቷቸዋል፡፡ በነሐሴ እና መስከረም ወራት ፖሊስ እና የአካባቢ ሚሊሺያ በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ አካባቢ ስድስት የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) አባላትን ካለፍርድ ቤት በመያዣ ትዕዛዝ ይዘው አስረዋል፡፡ የተያዙትም ሰዎች ሺፈራው ፈቃዱ፣ ፍቅሩ በንቲ፣ ምትኩ ተርፋ፣ አብርሃም ጅሬኛ፣ አብደታ አብርሃም፣ እና ሀብቱ ተሰማ ናቸው፡፡

የሥልጣን ተጋሪ የሆነው የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) ካድሬዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦፌዴን አባላትን ግንቦት 7 የፓርላማ ምርጫዎች በታዛቢነት ሲያገለግሉ በነበረበት ወቅት ያዋክቡዋቸው፣ ያሰፈራሩዋቸው ያግቱዋቸው እንደነበር ኦፌዴን ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ በአርሲ ዞን፣ አሳሳ ወረዳ ካድሬዎች ሼክ ማህሙድ ቱሱሩን ይዘው ለበርካታ ቀናት አግተዋቸዋል፡፡ ባለሥልጣኖች ለፓርላሜንት አዲስ የተመረጠውን የገበየሁ ሃያቶን ልጅ ከ10 ጊዜ በላይ ለምርመራ ጥያቄ ጠርተውታል፡፡ የኦፌዴን አባል የሆነው ሁሴን አደም በሶደሬ ወረዳ 20 ቀናት ታስሯል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በግንቦቱ ምርጫ በታዛቢነት ያገለገሉ ዘጠኝ የኦፌዴን አባላት በኢሉባቦር አውራጃ ገቺ ወረዳ እንደታገቱ ነበሩ፡፡ የአካባቢው ሹማምንት 10 የኦፌዴን አባላትን በባሌ ዞን፣ ናሲቦ ወረዳ ኮኮሳ ምርጫ ነጥብ ውስጥ ይዘው ማሰራቸውን ኦፌዴን ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አመልክቷል፡፡ እንደዚሁም በቦረና ዞን፣ ቡሌ ሆራ ወረዳ 13 አባላቱ መታገታቸውን ኦፌዴን ዘግቧል፡፡

የታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ከሱማሊያ እና ከኬንያ በመንደርደር ለሚያደርሱት ጥቃት ምላሽ በመስጠት፣ ወታደራዊው ክፍል አሰሳ ማካሄዱን ቀጥሏል፡፡ ይኸም በጋምቤላ፣ ሱማሌ፣ እና ኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ ጊዜ ከሕግ ውጭ የሆኑ እገታዎችን ያካተተ ነበር፡፡

በህዳር ወር የቅንጅት አባል እና የአዲስ አበባ ከንቲባ የሆኑትን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን እና ኘፎሬሰር መስፍን ወልደማርያምን ባለሥልጣኖቹ እንደገና አስረዋቸዋል፡፡

ለእነዚህ ሁለት ታዋቂ ምሁራን እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች መታሠር የተሰጠው ምክንያት ያለውን መንግሥት ለማስወገድ ያለመ ፀረ-መንግሥት ተቃውሞ እቅድ በማውጣት ተሳትፈዋል የሚል ነው፡፡ በዓመቱ መጨረሻ እነዚህ ሰዎች፣ ከበርካታ የሲቪክ ትምህርት ከሚሰጡ የመያድ አባላት እና ከነፃ ጋዜጠኞች ጋር በአገር ክህደት እና በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሰው እንደታሠሩ ነበሩ፡፡

ሌሎች ታዋቂ የሆኑ እና ተይዘው የታሠሩ የቅንጅት አመራር አባላት የሚከተሉት ናቸው፡- የቅንጅት ፕሬዚዳንት ኃይሉ ሻውል፣ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም፣ ቀደም ብሎ በሩዋንዳ ለተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፋዊ የወንጀል ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ የነበሩ፣ የቅንጅት ምክትል ፕሬዚዳንት ወ/ት ብርቱካን ሚደግሳ፣ ቀደም ብሎ ዳኛ የነበሩ፡፡ የእሥር ቤት ሕይወታቸው ይዞታ በቂ መሆኑ ተዝግቧል፡፡ በተለይ የቅንጅት መሪዎች የተለየ ክፍል እንደነበራቸው ነው የተነገረ፡፡ ሆኖም፣ የሕግ ምክር ማግኘት የቻሉት አልፎ አልፎ ብቻ ነበር፣ በቂ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘታቸውም በጣም የሚያሳስብ ነበር፡፡

በሚያዝያ እና በግንቦት 1996 ዓ.ም. የመኢዓድ አባላትን ከሕግ ውጭ ባገቱት የአማራ ክልል የመንግሥት ሚሊሺያ፣ የወረዳ ሹማምንት፣ እና ፖሊስ፣ ወይም ኦልባና ሌሊሳ የተባለውን የኦብኮ አባል ክስ ሳይመሠርትበት ከግንቦት እስከ ሐምሌ 1996 ዓ.ም. ከሕግ ውጭ ባገተው ፖሊስ ላይ ባለሥልጣኖቹ ምንም እርምጃ አልወሰዱም፡፡

በመቶዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞ ተማሪዎችን እና መምህራንን የኦነግ ደጋፊዎች ናቸው በሚል ጥርጣሬ በ1996 ዓ.ም. ለብዙ ሳምንታት በማገቻ ማዕከሎች ባገታቸው ፖሊስ ላይ ባለሥልጣኖች ምንም እርምጃ አልወሰዱም (1.ሐን ይመልከቱ)፡፡

በሺሕዎች የሚቆጠሩ የወንጀል ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት ለችሎት ሳይቀርቡ ለዓመታት ታግተው እንደሚገኙ ተዘግቧል፡፡ አንዳንዶቹ ታገቾች በኦሮሚያ ክልል በኦነግ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አላችሁበት ተብለው የተወነጀሉ፣ ወይም በየካቲት እና መጋቢት 1996 የተማሪዎች ሁከት ከተፈጠረ በኋላ የተያዙ መምህራን እና ተማሪዎች ናቸው፡፡

መንግሥት ክስ ሳይመሠርት በርካታ ሰዎችን፣ አንዳንዶቹን ለዓመታት፣ አግቶ ፖሊስ ጉዳያቸውን እየመረመረ ይገኛል፡፡ ወንድአንተ መስፍን፣ ሰው በመግደል ወንጀል ክስ ከተመሠረተበት በኋላ ባለፈው ሚያዝያ ባለሥልጣኖቹ የዕድሜ ልክ እሥራት በይነውበታል፡፡ ይህ ሰው ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ በደቡብ ጐንደር ነፋስ መውጫ ወህኒ ቤት ታግቶ የቆዬ ነው፡፡

ሠ. ትክክለኛ የሆነ ይፋ ዳኝነት መንፈግ

ሕጉ ነፃ የሆነ የሕግ ተርጓሜ/የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር ቢደነግግም፣ ፍርድ ቤቶች ደካማ እና የመዝገብ ጫና የበዛባቸው እንደሆኑ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች፣ በፍርድ ቤቶች ጉልህ የሆነ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እንዳለ ያምናሉ፡፡

መንግሥት ፍርድ ቤቶችን በፌዴራል መስመሮች አቅጣጫ መነጣጠሉን እና ዳግም ማዋቀሩን በመቀጠል፣ ፍርድ ቤቶችን በወረዳ፣ በዞን (ቀጠና) እና በክልል ደረጃ አቋቁሟል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ሕግን፣ ክልል ዘለል ጉዳዮችን እና ብሔራዊ ፀጥታን/ደህንነትን የሚመለከቱ መሠረታዊ እና የይግባኝ ጉዳዮችን በማየት ብይን ይሰጣሉ፡፡ የክልል የፍትህ ሥርዓቱ ራስ ገዝነቱ እያደር ተጠናክሯል፤ የየክልሉም ጉዳይ የሚሰማው በክልል ፍርድ ቤቶች ነው፡፡

የፌዴራሉ ፍትሕ ሚኒስቴር የክልል ቢሮዎች የአካባቢዎቻቸውን ፍትሕ ነክ ጉዳዮችን ተከታትለዋል፡፡ ፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥራ ባለመጀመራቸው አንዳንድ የክልል ፍ/ቤቶች ሁለቱንም ማለት የአካባቢና ፌዴራል ጉዳዮችን ዳኝተዋል፡፡ በአጠቃላይ፣ በክልሎች የሚታየው የፌዴራሉ የፍትሕ ሥርዓት እንቅስቃሴ ውሱን ነበር፡፡

ገጠመኞች እንደሚያመለክቱት ከሆነ፣ አንዳንድ የአካባቢ ባለሥልጣናት ከእነሱ በላይ ሥልጣን ያለው አካል እንዳለ አያምኑም፡፡ የክልል ሕጎች በሌሉበት ሁኔታ፣ ዳኞች የሚመሩት በፌዴራል የሥነ ሥርአት ሕግ እና መደበኛ ድንጋጌዎች ነው፡፡

የፍትሕ ሥርአቱ ያለበትን፣ ተመክሮ ያለው የሰው ኃይል የከፋ እጥረት ለማሻሻል፣ መንግሥት የበታች ፍ/ቤቶች ዳኞችንና አቃቢያነ ሕግ መመልመሉንና ማሠልጠኑን ቀጥሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተመደቡት የደመወዝ መጠኖች በተፈለገው ቁጥር ብቃት ያላቸው ባለሞያዎችን መሳብ እንዳልቻሉ ባለሥልጣናቱ ይናገራሉ፡፡

በሕጉ መሠረት የዳኝነት ሂደቶች፣ የተከሰሱ ሰዎች፣ "አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ" በፍርድ ቤት በይፋ የፍርድ ሂደት አድሎ የሌለበት ፍትሕ የማግኘት፣ እስኪፈረድባቸው ድረስ ከተከሰሱበት ወንጀል ንጹሕ እንደሆኑ የመቆጠር፣ በመረጡት ጠበቃ የመወከል እና ይግባኝ የመጠየቅ መብቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ ዝግ ችሎቶች ተካሄደዋል፤ አንዳንድ ጊዜ፣ ባለሥልጣናቱ ታሣሪዎች ከጠበቃዎቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት አጭር እንዲሆን አድረገዋል፣ ወይም ጭራሹን ከልክለዋቸዋል (ክፍል 1.መን ይመልከቱ)፡፡

በተጨማሪም ታሣሪዎች በአብዛኛው ከተከሰሱበት ጥፋት ንጹሕ ተደርገው አይቆጠሩም ነበር፡፡ አቅም ለሌላቸው፣ መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ በተጨባጭ ግን የዚህ አሠራር ተግባራዊነት በተለይ በልዩ አቃቤ ሕግ የተከሰሱትን በተመለከተ በጣም ውሱን ነው፡፡ ምንም እንኳ በሙስና የተከሰሱ ሰዎች ለዳኝነቱ ሂደት ጽ/ቤት ከመቅረባቸው በፊት የክሱ ጭብጥ ማስረጃዎች እንዲሰጧቸው ሕጉ በግልጽ ቢያስቀምጥም፣ ባለሥልጣኖቹ ክርክሩ እስኪጀመር ይህን የተከላካይ ጠበቃዎች እንዳያገኙ ማድረግ እንደ መደበኛ አሠራር ይጠቀሙበታል፡፡

ሕጉ ቀደም ሲል ለነበሩ የሃይማኖትና የባህል ፍ/ቤቶች ሕጋዊ አቋም ከመስጠቱም በላይ፣ የፌዴራልና የክልል ሕግ አውጪዎች ለሌሎች ፍ/ቤቶች ዕውቅና እንዲሰጡ ይፈቅዳል፡፡ በሕግ፣ አንድ ክርክር የሚመለከታቸው አካላት፣ ጉዳዩን የሚዳኘው የባህል ወይም የሃይማኖት ፍ/ቤት እንደሚሆን አስቀድሞ መስማማት ይገባቸዋል፡፡ የሻሪያ (እስላም) ፍ/ቤቶች ሙስሊሞችን የሚመለከቱ ሃይማኖታዊና ቤተሰባዊ ጉዳዮችን መዳኘት ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሽማግሌዎች ጉባኤዎችን የመሰሉ ሌሎች ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ግልጋሎታቸውን ቀጥለዋል፡፡ የሕግ ሽፋን ባይኖራቸውም፣ እነዚህ ባህላዊ ፍ/ቤቶች በገጠር ለሚኖሩና ዘመናዊ የፍርድ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ላልሆኑ ብዙሃኑ ዜጐች ክርክሮችን ፈተዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሰባተኛ ችሎት፣ ሴቶችንና ሕፃናትን የሚመለከቱ የወሲብ ጥቃት ክሶችን አይቷል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ፍ/ቤቱ 541 ክሶችን ተቀብሎ በ351 ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የታዳጊ ጥፋተኞችን (juvenile) የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ ለመስማት ሶስት የፌዴራል ዳኞች በችሎቱ ተሰይመዋል፡፡ እነዚህ መዝገቦች እጅግ ተጓተው ስለነበረ፣ ጉዳያቸው እስከሚሰማ የተከሰሱ ሕፃናት በአብዛኛው ከአዋቂዎች ጋር በእስራት ቆይተዋል፡፡

ወታደራዊው የፍትሕ ሥርዓት በየጊዜው የሚጨምሩትን መዝገቦች ለማስተናገድ በብቃት የሠለጠነ የሰው ኃይል የለውም፡፡ ወታደራዊ የፍትሕ ሠራተኞችን ለማሠልጠን የውጭ ዕርዳታ በዓመቱ ቀጥሏል፡፡ በመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት ወይም በሌላ ስሙ በደርግ አገዛዝ፣ ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጠያቂ የሆኑትን ለፍርድ ለማቅረብና በሥልጣን፣ በመባለግ የተፈጸሙ ጥፋቶችን በመመርመርና ለፍትህ አቅርቦ ለታሪክም ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ለማድረግ እአአ በ1992 ስለተቋቋመው የልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት እንቅስቃሴዎች አዲስ መረጃ አልነበረም፡፡ በደርግ ዘመነ መንግሥት በተፈጸሙ ጥፋቶች የተከሰሱ በግምት አንድ ሺሕ የሚሆኑ ሰዎች በእስራት ቆይተዋል፡፡ አልፎ አልፎ በቂ ችሎታና ልምድ የሌላቸውና በፍርድ ቤት የተሰየሙ ጠበቃዎች እነዚህኑ ተከሳሾች ወክለዋቸዋል፡፡

የፖለቲካ እስረኞች

በዓመቱ የነበረው የፖለቲካ እስረኞች ጠቅላላ ቁጥር በአያሌ ሺሕዎች ይገመታል፡፡

ምንም እንኳ ተጠርጣሪዎች በ48 ሰአት ውስጥ ፍ/ቤት ቀርበው ክሳቸውን እንደሚሰሙ ሕጉ ቢደነግግም፣ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ፣ የሲቪል ማህበራት መሪዎችና ጋዜጠኞች ፍ/ቤት ሳይቀርቡ፣ ከጠበቃዎችና ቤተሰቦቻቸው ጋር ሳይገናኙ ለብዙ ቀናት ታስረዋል፡፡ ፖሊስና የአካባቢ ሚሊሺያዎች ለምርመራ ብለው በሺሕ የሚቆጠሩ ሰዎችን ለአያሌ ቀናት በፖሊስ ጣቢያዎችና የማገቻ ሰፈሮች እንደቆዩ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች (ቅንጅት ለአንድነት ለዲሞክራሲ፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊያን ኃይሎች ሕብረት እና የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ) አመልክተዋል፡፡

ረ. በግል ሕይወት፣ በቤተሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በመጻጻፍ የማን አለብኝነት ጣልቃ ገብነት

የግል ንብረቶችን ለመበርበር፣ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት የፍርድ ቤት ማዘዣ እንዲኖራቸው ሕጉ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም፣ በተግባር፣ በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ፤ ፖሊሶች ብዙውን ጊዜ የፍርድ ቤት ማዘዣ ሳይዙ የግል ንብረቶችን በርብረዋል (ክፍል 1.መ.ን ይመልከቱ)፡፡ ያለአግባብ ገንዘብ መውሰድን ጨምሮ፣ ፖሊሶች አንዳንድ ጊዜ በሀሰት ማዘዣ በመጠቀም ወደ መኖሪያ ቤቶች በመግባት ሕገ ወጥ ድርጊቶች እንደፈጸሙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወካዮች ተናግረዋል፡፡ በሃሰተኛ ማዘዣዎች መጠቀምን ጨምሮ፣ የፌዴራል ፖሊሶች ሰዎችን እንደዘረፉ በዓመቱ ተዘግቧል፡፡

ፖሊሶች ወደ ሰላማዊ ሰዎች ቤቶች በኃይል የመግባታቸው ዘገባዎች ቀጥለዋል፡፡ በሰኔ እና በሀዳር ወር መጀመሪያ ላይ በተከሰቱት ሰላማዊ ሰልፎች ወቅትና እነሱንም ተከትሎ፣ የፀጥታ ኃይሎች ወደ መኖሪያ ቤቶች በመግባት ያለፍርድ ቤት ማዘዣ የግል ንብረቶችን በርብረዋል፣ ያለፍርድ ቤት ማዘዣ በሺሕ የሚቆጠሩ ሰዎችን በሌሊት ከቤታቸው ወስደዋል፣ አብዛኛውን ጊዜም የቤተሰብ አባላትን ወይም ሌሎች በቦታው የተገኙትን አስረዋል፡፡

አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤታቸውን እንዳቃጠሉባቸውና ቢሯቸውን እንደዘረፉባቸው አሳውቀዋል (ክፍል 3ን ይመልከቱ)፡፡

የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ተቋማት በሙሉ የመንግሥት ነበሩ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎችና አንድ የውጭ ዲፕሎማት የስልክ ጠለፋና ሌላም ዓይነት የኤሌክትሮኒክ ጆሮ መጥባት (eavesdropping) ድርጊቶችን አስመዝግበዋል፡፡

የተወሰኑ ግለሰቦችን እንቅስቃሴዎች እየተከታተሉ መረጃ እንዲያቀብሉት፤ መንግሥት ሰላዮችን ቀጥሮአል፡፡ በዓመቱ ውስጥ በገጠር ቤተሰቦችን ከመኖሪያቸው በግድ የማፈናቀል ዘገባዎች ነበሩ፡፡ ቤተሰቦችን ለድርቅ ከተገላጡ ወደ ለም አካባቢዎች የማዛወር የሠፈራ ፕሮግራም መንግሥት በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነበር ይላል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበኩላቸው፣ በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ባለሥልጣናት፣ የሠፈራ መዝገቦችን በማዛባት የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን ለሠፈራ ይዳርጋሉ ሲሉ ከሰዋል፡፡ ድንበር የለሽ ሐኪሞችን (Doctors Without Borders) የመሰሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) እንደዘገቡት፣ በአንዳንድ የሠፈራ ፕሮግራሙ ክንዋኔዎች፣ መንግሥት ሰዎችን መሠረተ ልማቶችና የንፁሕ ውሃ አቅርቦት በሌለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች አስፍሯቸዋል፡፡ ይህም ከተለመደው በላይ ከፍተኛ የሆነ የሕፃናት ሞት አስከትሏል፡፡ በተወሰኑ የኦሮሚያ፣ የአማራና የደቡብ ክልሎች፣ ለገዥው ፓርቲ ድጋፍ ለማስገኘት ሲባል የአካባቢ ባለሥልጣናት የመሬት ሽግሽግንና የምግብ ዕርዳታ መንሳትን እንደማስፈራሪያ እንደተጠቀሙ ከኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጉባኤና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ታማኝ ዘገባዎች በዚሁ ዓመት ቀጥለዋል፡፡ ግለሰቦች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባል እንዳይሆኑና ንብረታቸውንም ለእነዚህ አካላት እንዳያከራዩ ለመከልከል በገዥው ፓርቲ ወይም በመንግሥት ስለሚደረጉ ወከባዎች በርካታ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ ድብደባ፣ ቤት ማቃጠልንና ግድያን (ክፍል 1.ሐ፣ 1.መ.፣ 3 እና 5ትን ይመልከቱ) ጨምሮ፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ላይ ያነጣጠሩ፣ ብዛት ያላቸው እና ከዚህም ስለባሱ ወከባዎችና ጥቃቶች ዘገባዎች ነበሩ፡፡

እንደዚሁም መምህራንና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባል በመሆናቸው ቅጥራቸው ስለመቋረጡ ታማኝ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ እንደ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት (ደኢሕዲሕ-SEPDC) ተቃዋሚ ፓርቲ፣ የክልሉ አስተዳደር የደኢሕዲሕ አባላትን፣ በተለይ መምህራንን ከሥራ ማባረሩን ቀጥሏል፡፡

ፍችን ወይም ከተጋቢዎች አንዱን ሞትን ተከትሎ፣ እንደገና ለማግባት ስድስት ወር መቆየት እንደሚያስፈልግ በሕግ ተደንግጓል፡፡ መንግሥት፣ ይህ የመቆያ ጊዜ ያስፈለገው ሴቷ ከሟች ባሏ መጸነሷን ወይም አለመጸነሷን ለመወሰን ነው ብሏል፡፡

ጋብቻውን የሚያከናውነው ባለሥልጣን በፊት ከነበረ ጋብቻ ሴቷ አለመጸነሷን ለማሳየት የዕርግዝና ምርመራ እንድታደርግ መጠየቅ ቢችልም፣ ሕጉ በተግባር በሥራ ላይ አልዋለም። አንድ ጋብቻ ለምን በመቆያው ጊዜ ውስጥ እንደተፈጸመ፣ ይመለከተኛል ያለ ማንኛውም አካል በጽሑፍ ይፋ ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል።

በመንግሥት ለጥያቄ የተፈለጉ ሰዎች ቤተሰብ አባላትን የፀጥታ ኃይሎች በእስራት ማቆየታቸውን ቀጥለዋል።

ክፍል 2፡- የሲቭል ነፃነቶችን ማክበርን ጨምሮ፡-

ሀ. የመናገርና የኘሬስ ነፃነት

በሕግ የመናገርና የኘሬስ ነፃነት አለ፤ በተግባር ግን መንግሥት እነዚህን መብቶች ገድቧል። መንግሥት እንደሚለው የፈጠራ መረጃ በማሰራጨታቸውና ሌሎችን የኘሬስ ሕግ መተላለፍን በመፈጸማቸው መንግሥት ጋዜጠኞችን፣ አሳታሚዎችንና አዘጋጆችን ማዋከቡንና መክሰሱን ቀጥሏል። መንግሥት የብሮድካስት ሚዲያን በሙሉ ተቆጣጥሯል። ራስን በራስ ሳንሱር ማድረግ በግልና በመንግሥት ጋዜጠኞች የተለመደ አሠራር ሆኗል።

ከግንቦት 7/1997 ምርጫ በፊት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉት መገናኛ ብዙሀን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ለተቃዋሚ አመለካከት ክፍት ነበሩ። ከምርጫው በኋላ ግን በአጠቃላይ ያንፀባረቁት የመንግሥትንና የገዥውን ፓርቲ የኢሕአዴግን መስመር ብቻ ነበር። በመንግሥትና በግሉ ኘሬስ መካከል ግንኙነቱ በአብዛኛው ተካሯል።

የውጭ ጋዜጠኞች ሥራቸውን በነፃ ቀጥለዋል፤ ብዙ ጊዜም የመንግሥትን ፖሊሲዎች በመተቸት ጽፈዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በነፃነት ከሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች ይልቅ የውጭ ጋዜጠኞችን እና የመንግሥት አፍቃሪ የሆኑ የአገር ውስጥ ጋዜጠኞችን ብዙውን ጊዜ በበለጠ አቅርበዋል። ይሁን እንጂ ከግንቦት 7 ብሔራዊ ምርጫ ቀደም ሲል፣ ጥቂት ዓለምአቀፍ ዘጋቢዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ ከመንግሥት በኩል ጠንካራ ተጽዕኖ እንደነበረባቸው ተናግረዋል። እነሱም የተጠየቁትን ለማድረግ እምቢ ቢሉም፣ ወዲያውኑ የደረሰባቸው ምንም ነገር አልነበረም።

የግል ሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲኖሩ ሕግ የወጣ እና መንግሥትም ለአዳዲስ ጣቢያዎች ፈቃድ እሰጣለሁ ቢልም፣ መንግሥት ሁሉንም የሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭት ሚዲያ መቆጣጠሩን ቀጥሏል። መንግሥት ብቸኛውን የቴሌቭዥን ጣቢያ ስርጭት ያካሄዳል፣ በዚህም የዜና ስርጭትን በጥብቅ ይቆጣጠራል።

የብሮድካስት ሕጉ የፖለቲካና ሃይማኖት ድርጅቶች የራሳቸው የስርጭት ጣቢያዎች እንዳይኖራቸው ይከለክላል፡፡ ሕጉ የእነዚህን ተቋማት በውጭ ባለቤትነት መያዝም ይከለክላል፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር የሚካሄደው የኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለኘሮግራምና ለማስታወቂያ፣ የስርጭት ጊዜ መግዛት ለፈለጉ የግል አካላትና ግለሰቦች ይህንኑ ሸጧል፡፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ የደቡብ ሬዲዮ ድምፅ በሚል መጋቢት 23 ቀን 1997 ባቋቋመው ክልላዊ የኤፍኤም ሬዲዮ ጣቢያ በቀን ለአንድ ሰዓት በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፍ ስርጭቱን ጀምሯል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርም በቀን ለአምስት ሰዓት የሚተላለፍ የኤፍኤም ስርጭት የሙከራ ኘሮግራሞችን ጳጉሜ 1997 ጀምሯል፡፡

ዓለምአቀፍ የዜና ስርጭቶችን በመቀበል ላይ ገደቦች ነበሩ፡፡ የቢቢሲ እና የዶቼ ቪሌ (የጀርመን ድምፅ) ስርጭቶች በአገሪቱ ዙሪያ ተደምጠዋል፡፡ በኢንተርነትም የተቃዋሚ ድረ-ገጾችን መቃኘት ይቻል ነበር፡፡ በዓመቱ መጨረሻ የአሜሪካ ድምፅ (Voice of America) የሬዲዮ የስርጭት ሆን ተብሎ በሚደረግ አፈና (jamming) እንዳይሰማ ተደርጓል፡፡ መንግሥት የግል የሳተላይት መቀበያ ዲሾችን (satellite receiving dishes) ባለቤትነት ፈቅዷል፡፡ ሆኖም፣ የወጪዎቹ መናርና የኢትዮጵያ ቴሌክሙኒኬሽንስ ኮርፖሬሽን የተሰኘው ብቸኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ባለቤት ውሱን አቅም፣ በዚህ ቴክኖሎጂ መጠቀምን በተግባር ገድበውታል፡፡ የሀሰት መረጃ ስለማተም፣ በብሔረሰቦች መካከል ጥላቻን ስለመቀስቀስ፣ ስም ስለማጥፋት እና የሕብረተሰቡን የሞራል እሴቶች የሚፃረሩ ጽሑፎችን ስለማውጣት በተቀመጡ የሕግ አንቀጾች በመጠቀም መንግሥት ጋዜጠኞችን መያዝና ማሰሩን ቀጥሏል፡፡ የመረጃ ምንጮችን እንዲያወጡ ተጽዕኖ ለማድረግም ባለሥልጣኖች ጋዜጠኞችን አስረዋቸዋል፡፡ በእነዚሁም ላይ የሚያቀርባቸውን ክሶች ሕጋዊ ለማድረግ፣ መንግሥት ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተወሰኑ ክፍሎችን እየመረጠ እንደሚጠቀም ነፃ ጋዜጠኞች መንግሥትን ከሰዋል፡፡

በዓመቱ ውስጥ መንግሥት ብዛት ያላቸውን ጋዜጠኞች ከሷል፤ አስሯል፤ በገንዘብም ቀጥቷል፡፡

ጥር 3 የመንግሥት ንብረት በሆነው የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የኦሮምኛ ቋንቋ አገልግሎት ጋዜጠኛ የነበረው ሽፈራው እንሰርሙ ተይዞ ለሶስተኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ማዕከላዊ ምርመራ ጽ/ቤት ታስሯል፡፡

የመንግሥትን መረጃ ለኦሮሞ ነፃነት ግንባር አመራር አሳልፋችሁ ሰጥታችኋል የሚለውን ጨምሮ በአያሌ ክሶች የተወነጀሉት ሽፈራውና በሚያዝያ 1996 (April 2004) የተያዘው ባልደረባው የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ጋዜጠኛ ዳበሳ ዋቅጅራ እንደታሰሩ ቆይተዋል፡፡ ሁለቱ ግለሰቦች እንዲፈቱ በፍርድ ቤት የተሰጡ የተለያዩ ትዕዛዞችን የእስር ቤቱ ባለሥልጣኖች ቸል ብለዋቸዋል፡፡

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መሪዎችን ለመያዝና ለመግደል ኢሕአዴግ ልዩ የስለላ ኃይል ማቋቋሙን የዘገበው የግንቦት 9 ቀን መጣጥፍ እና የቅንጅት መሪዎችን በመርዝ እንዲያከስሙ 11 የትግራይ ሴቶች መመልመላቸውን ጨምሮ፣ የሁለት ዘገባዎች ምንጮችን እንዲገልጽ፣ የአዲስ ዜና ዋና አዘጋጅ፣ ፋሲል የኔዓለምን፣ ፖሊስ ጠይቆት ነበር፡፡ ፋሲል ምንጮቹን ለመግለጥ ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣ ሊረጋገጥ የማይችል ዜና አሳትመሃል ተብሎ ታስሯል፡፡

ግንቦት 30 ቀን የግንቦት 7 ምርጫን በሚመለከት ሚዛናዊ ያልሆኑ ዘገባዎችን አቅርባችኋል ተብለው በመከሰስ፣ ለውጭ ሚዲያ የሚሠሩ ሔለን ሞሐመድ፣ ተማም አማን፣ በረከት ተክሉ፣ ታደሰ እንግዳውና አሰገደች ይበርታ የሚባሉ አምስት ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች የሥራ ፈቃዳቸውን የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠርዟል፡፡

የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በአዲስ አበባ የጋዜጣ አከፋፋይ የሆነውን ፍቅሬ ጉዱን ሰኔ 1 ቀን ይዘው ለአንድ ወር አግተውታል፡፡ በሰኔ 30 ከተፈታ በኋላ ፍቅሬ በፀጥታ ኃይሎች ስለመያዙና በኋላም ከዋና ከተማ ወጣ ባለ የማገቻ ማዕከል ስለመታሰሩ "አስኳል" ለተሰኘው ሳምንታዊ የአማርኛ ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ ሰጥቷል፡፡ በዚህም መጥፎ የእስር ቤት ሁኔታዎችን ከመዘርዘሩም በላይ፣ ስለመታሠሩም መንግሥትን ተችቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ባለሥልጣኖቹ ፍቅሬን ነሐሴ 13 ቀን ይዘው እንደገና ካገቱት ከአራት ቀን በኋላ በዋስ ለቅቀውታል፡፡ በዚህ የቅርብ ጊዜ እስራቱም፣ ቃለ መጠይቁን የሀሰት መረጃ ለማሰራጨትና የፖሊስንና የእስር ቤቶች ሥርዓትን ስም ለማጉደፍ ተጠቅመህበታል በማለት ፖሊስ ፍቅሬን ከሶታል፡፡

የሰው ሕይወት በጠፋባቸው በወሩ መግቢያ ላይ በተከሰቱት ፀረ-መንግሥት ሰላማዊ ሰልፎች እጃችሁ አለበት ያላቸውን፣ 12 ጋዜጠኞችን ጨምሮ፣ የ58 ሰዎች ስም ዝርዝር መንግሥት በሀዳር ወር አውጥቷል፡፡ በዚሁ ወር ውስጥ ፖሊስ ከጋዜጠኞቹ ስድስቱን አስሯል፡፡ የታሰሩ ተቀዋሚዎችና ጋዜጠኞች በአገር ክህደት፣ በዘር ማጥፋትና ሕገመንግሥቱን ለመፃረር ሙከራ በማድረግ ተከሰዋል፡፡ እነዚህ ክሶች

ጥፋተኛ ሆነው በተገኙት ላይ የእሥራትና እስከሞት ቅጣት የሚደርስ ብያኔ ሊያሰጡ የሚችሉ ናቸው፡፡

በዓመቱ መጨረሻ የታሰሩት ጋዜጠኞች ፍ/ቤት ለመቅረብና ክሳቸውን ለመስማት አሁንም በመጠበቅ ላይ ነበሩ፡፡ የጋዜጠኞች መታሰር ተጨማሪ ውጤት፤ ከጠቅላላው የአማርኛ ጋዜጦች ስርጭት 80 ከመቶውን የሚወክሉትን ከ12 በላይ የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጦችን መዘጋት ነበር፡፡

ዓመቱ ሲገባደድ፣ አንድ ጋዜጠኛ የአንድ ወር እስራት ተበይኖበት ተፈቷል፣ ከ34 በላይ ተጠርተዋል፣ ተጠይቀዋል፣ ተይዘዋል፣ ከኘሬስ ጋር በተያያዘ ውንጀላ ታስረዋል፤ ከ58 እስከ 346 ዶላር (ከብር 500-3000) የሚደርስ ዋስትና እንዲከፍሉ ተደርገዋል፤ በግምት 54 የሚሆኑ ጋዜጠኞች በስደት ቆይተዋል፤ በአገር ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ጋዜጠኞች በወንጀል ተከሰዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ሁለት የመንግሥት ሚዲያ ጋዜጠኞች፣ ከኘሬስ ይልቅ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ክስ በእስር ቆይተዋል፡፡

ሁሉም የመንግሥት ሚዲያዎች የመንግሥት ድጐማ አግኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሚዲያዎች፣ በሕግ ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሆነው ለራሳቸው አመራር እና የሚያስፈልጋቸውን ገቢ በከፊል ለማግኘት ኃላፊነት ነበረባቸው፡፡

የማስታወቂያ ሚኒስትሩ የመንግሥት ኦፊሴል ቃል አቀባይ ሆኖ ሲሠራ፣ ሚኒስቴሩም በመንግሥት፣ በኘሬስና በሕዝብ መካከል የሚደረገውን ግንኙነት ሲመራ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ከግሉ ኘሬስ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሳያሰልስ እምቢ ከማለቱም ባሻገር፣ ከኘሬሱ ጋር የሚያደርገው ትብብር ብዙውን ጊዜ በመንግሥት ከሚተዳደረው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ ኢሕአዲግ ከሚቆጣጠረው ዋልታ መረጃ ማዕከል እና ከዓለምአቀፋዊ የዜና አገልግሎት ድርጅቶች ሪፖርተሮች ያለፈ አልነበረም፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት የሚካሄዱትን ይፋ እንቅስቃሴዎች ለመከታተል እንኳን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ነፃው ኘሬስ እንዳይገኝ መከልከሉን ቀጥሏል፡፡ የዚህ ዓይነቱን እንቅስቃሴ እንዲሸፍኑ የሚፈቀድላቸው የመንግሥት ዜና አውታሮች ተወካዮች ናቸው፡፡

ሪፖርተሮች ዘወትር ራሳቸውን በራሳቸው ሳንሱር እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

ጋዜጦች በየዓመቱ የህትመት ፈቃዳቸውን ሲያድሱ፣ በባንክ ተቀማጭ ሂሣባቸው ብር 10,000 (1,150 ዶላር) እንዲኖራቸው የማስታወቂያ ሚኒስቴር አስገድዷቸዋል፡፡

የገንዘቡ መጠን በግብር ትናንሽ ጋዜጦችን ከምዝገባ ውጭ አድርጓቸዋል፡፡ እንደዚሁም አሳታሚዎች ጋዜጣ ለማቋቋምና ሥራውን ለማካሄድ ቋሚ ኬሪነት እንዲኖራቸው ባለሥልጣኖች ይጠይቃሉ፡፡

መንግሥት ከሌሎች የንግድ ሥራ ባለቤቶች ተመሳሳይ ግዴታ ስለማይጠይቅ፣ አንዳንድ ነፃ ጋዜጠኞች እንደሚሉት የኬሪነቱን ግዴታ መንግሥት ጋዜጦችን ማስቸገሪያ ዘዴ አድርጐ ተጠቅሞበታል፡፡ የኘሬስ ሕጉ፣ አሳታሚዎች ሁሉ የጎትመቶቻቸውን ቅጅዎች በታተሙበት ቀን ለማስታወቂያ ሚኒስቴር በነፃ እንዲሰጡ ያስገድዳል፡፡

ከግል ጋዜጦች አብዛኞቹ እና እንደዚሁም የመንግሥት ጋዜጦች የሚታተሙት በመንግሥት በተያዙ ማተሚያ ቤቶች ነበር፡፡ የህዳሩን አለመረጋጋት ተከትሎ፣ ማተሚያ ቤቶች ጥቂት ጋዜጦችን ማተም እምቢ ብለዋል፡፡ እንደምክንያት የሰጡትም ለሚያትሟቸው ጎትመቶች ይዘት ተጠያቂ እንደሚሆኑ የሚያመለክቱ የፍትሕ ሚኒስቴር መግለጫዎችን ነበር፡፡ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማንኛውንም ማተሚያ ቤት መዝጋት እንደሚችል ፖሊስ ሥልጣን ቢኖረውም፣ በዓመቱ ውስጥ ፖሊስ ይህን ሥልጣን ተግባራዊ አላደረገውም፡፡

በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተሙ ጋዜጦች መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎች ማውጣታቸው ቀጥለውበታል፡፡

የፍትሕ ሚኒስቴርን ይግባኝ በመሻር፣ የኢትዮጵያ ነፃ ኘሬስ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) ሕጋዊ እውቅና አለው ሲል በታህሣሥ 1996 የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማጽደቅ፣ የካቲት 24 (March 3)፣ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኢነጋማ ላይ ለ17 ወራት ተጥሎ የነበረውን እገዳ አንስቷል፡፡

ኘሬዝዳንቱ፣ ጋዜጠኛ ክፍሌ ሙላት እንዲያዝ በመንግሥት ከሚፈለጉት ጋዜጠኞች መካከል ስለነበር፣ በዓመቱ መጨረሻ ማህበሩ በእንቅስቃሴ ላይ አልነበረም፡፡ በህዳሩ ግርግር ወቅት ከነበረበት ወደአገሩ ባለመመለሱ፣ ክፍሌ ከእስራት አምልጧል፡፡ በመንግሥት ደጋፊነት (sponsored) ከኢነጋማ ጋር አንድ ዓይነት ስም ያለው ተፎካካሪ ማህበር በዓመቱ ውስጥ እንቅስቃሴ አላደረገም፤ የሚገኝበት አቋምም አልታወቀም፡፡

ዓመቱ ሲገባደድ፣ በ1995 በማስታወቂያ ሚኒስቴር የተዘጋጀው ረቂቅ የኘሬስ ሕግ በይፋ ለፓርላማ አልቀረበም፡፡ ሆኖም፣ መጋቢት 19 ቀን ፓርላማ፣ ከረቂቅ የኘሬስ ሕጉ ውስጥ ቅጣታቸው እጅግ የከፉትን አንቀጾች በግንቦት ወር፣ ሥራ ላይ በዋለው አዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል፡፡ አንቀጾቹ ሁሉንም ጥፋቶች የሚመለከቱ አጠቃላይ ድንጋጌዎችንና የተለዩ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይጨምራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በኘሬስ ለተፈጸሙ ጥፋቶች ተጠያቂነትን የሚመለከቱና ከረቂቁ የኘሬስ ሕግ ቃል በቃል የተወሰዱ አንቀጾች ይገኙባቸዋል፡፡

ጋዜጠኞችና ዓለምአቀፍ የሚዲያ ድርጅቶች ረቂቅ ሕጉን ነቅፈውታል፡፡ በምክንያት የጠቀሱትም አሻሚነቱን ወይም ግልጽነት የጐደለው መሆኑን፣ ገደቦቹን፣ ከባድ ቅጣቶቹንና ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ከልክ ያለፈ ሥልጣን መስጠቱን ነበር፡፡ የኘሬስ ሕጐችን እንደገና ለማርቀቅና ለማሻሻል እንዲያግዙ፣ የሚዲያ ባለሞያዎች እንዲያቀርቡለት መንግሥት ዓለምአቀፍ ለጋሾችን ጠይቋል፡፡

መንግሥት በኢንተርኔት መጠቀምን አልገደበም፡፡ ቢሆንም፣ የሰኔ 1 ቀን ሁከትን ተከትሎ፣ የመንግሥቱ የቴሌኮሙኒኬሽን ሞኖፖል በሞባይል ስልክ የጽሁፍ መልዕክት መቀባበልን (mobile-phone text messaging) ከጥቅም ውጭ አድርጐታል፡፡ ለዚህ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ለዘለቀው የአገልግሎቱ እገዳ የተሰጠው ምክንያት ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፀረ-መንግሥት ቅስቀሳዎችን ለማካሄድ ይጠቀምበታል የሚል ነበር፡፡

በዓመቱ ውስጥ መንግሥት የትምህርት ነፃነትን ገድቧል፡፡ መንግሥት እንደሚለው ምሁራን በተሰማሩበት የጥናት መስክ ምርምር ማድረግ ቢችሉም፣ የፖለቲካ ስሜቶችን ግን ሊያስተናግዱ አይችሉም፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ መምህራን በይፋ ከተቀመጠው ሥርዓተ ትምህርት እንዳይወጡ ከመከልከላቸውም በላይ፣ በዩኒቨርሲቲ ቅፅር ግቢዎች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች እንዳይኖሩ ባለሥልጣኖቹ ተከላክለዋል፡፡ ጥቂቶቹ የሰኔ ሁከቶች የተከሰቱት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅፅር ግቢ እና በአካባቢው፣ እንዲሁም በአንድ የመንግሥት የተግባረ ዕድ ት/ቤት ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ሲል መለዮ የለበሱ እና ያልለበሱ የፖሊስ አባላት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቅፅር ግቢዎች ውስጥ እንደነበሩ ተዘግቧል፡፡ በዓመቱ ውስጥ መንግሥት ተማሪዎችንና መምህራንን አስሯል (ክፍል 1.መን ይመልከቱ)፡፡

ለ. ሰላማዊ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት

የመሰብሰብ ነፃነት

ሕጉ የመሰብሰብ ነፃነትን ይፈቅዳል፡፡ ከምርጫዎች በፊት በነበረው የሳምንት መጨረሻ በአዲስ አበባ የተደረገውን ወደ አንድ ሚሊዮን ሰዎች የተገኙበትን ሰላማዊ ሰልፍ ጨምሮ፣ ከግንቦት 7 ብሔራዊ ምርጫ ቀደም ሲል በርካታ የተቃዋሚዎች የአደባባይ ስብሰባዎች (rallies) ተደርገዋል፡፡ የትላልቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና የሰላማዊ ሰልፎች አዘጋጆች ከ72 ሰዓታት ቀደም ብለው ለመንግሥት ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘ ት አለባቸው፡፡ በዓመቱ ውስጥ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረቡ የፈቃድ ጥያቄዎች ስለመነፈጋቸው አያሌ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የክልል ባለሥልጣኖች ያለበቂ ምክንያት ወይም መግለጫ ፈቃድ መስጠት ለረጅም ጊዜ እንደዘገየ እና በመጨረሻዋ ደቂቃም እንደሰረዙ ገልጽዋል፡፡ ነፃው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ስብሰባዎችንና ሰላማዊ ሰልፎችን ለማካሄድ ያደረገው ሙከራ በመንግሥት መታገዱ ቀጥሏል፡፡ በብሔራዊ ምርጫዎች ዋዜማ ግንቦት 6 ቀን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአንድ ወር የሚጸና ሆኖ በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ ማንኛውንም ዓይነት ሰላማዊ ሰልፍ አገዱ፡፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ እገዳው የዜጐችን ሕገመንግሥታዊ መብቶች መጋፋት ነው በማለት በግንቦት 17 መግለጫው አውግዞታል፡፡

እገዳው እስከ ነሐሴ 7 የተራዘመ ቢሆንም፣ ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 1 ሰላማዊ ሰልፈኞች መንግሥትን መቃወማቸው፣ በአዲስ አበባ ቢያንስ 42 ያልታጠቁ ሰልፈኞች በፀጥታ ኃይሎች መገደልን አስከትሏል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተከሰተውን ሁከት ተከትሎ፣ ግንቦት 29 የየካ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የነበረችውን ሽብሬ ደሳለኝንና የኮተቤ መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ተማሪ የሱፍ አብደላን ፖሊስ ተኩሶ ገድሏል፡፡ የ16 ዓመቱ የኮልፌ ክፍለ ከተማ ተማሪ ነብይ ዓለማየሁንና የሰባት ልጆች እናት የሆነችውን ዙሉፋ ሱሩርን ሰኔ 1 ቀን ፖሊስ ተኩሶ ሲገድል፣ ሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ወንድማማቾች የሆኑትን ፈቃዱ ነጋሽንና አብርሃም ይልማን (ዕድሜ 16) ገድለዋል፡፡ የሰኔ 1 ቀኑን "ሕገ ወጥ ሰልፍ" ተከትሎ 26 ሰዎች መሞታቸውን ፌዴራል ፖሊስ አምኗል፡፡ በግድያዎች ዙሪያ የነበሩትን ሁኔታዎች የሚመረምር ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን መንግሥት አቋቁሟል፡፡

በጥቅምት 22 አና 28 ቀን መካከል፣ የጦር ሠራዊትና የፖሊስ ኃይሎች በአዲስ አበባ ድንጋይ በሚወረውሩ ሰልፎኞች ላይ ተኩስ ከፍተው ቢያንስ 40 ግለሰቦችን ገድለዋል (ክፍል 2.ለን ይመልከቱ)፡፡

መንግሥት አንዳንድ ሰልፈኞች ገጀራና የእጅ ቦምብ ታጥቀው ነበር ብሏል፡፡ አማራና ኦሮሚያን ጨምሮ፣ በአገሪቱ ዙሪያ በብዙ አካባቢዎች፣ በተቃዋሚ ሰልፈኞችና በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፖሊስ መካከል የተደረጉ ፍጥጫዎች ለበርካታ ሰዎች መሞት ምክንያት መሆናቸውን በርካታ ክልሎች ዘግበዋል፡፡

በመስከረም ወር በተለያዩ ከተማዎች ያቀዷቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች በአካባቢዎቹ ባለሥልጣኖች መከልከላቸውን ቅንጅት እና ሕብረት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ሕብረት) ለመስከረም 19 ቀን የጠራው የአባላቱ ጠቅላላ ጉባኤ፣ መንግሥት በአዲስ አበባ ለሚገኙ ባለሆቴሎች አዳራሾቻቸውን ለሕብረቱና ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳያከራዩ መመሪያ በመስጠቱ፣ ለመሰረዝ መገደዱን አስታውቋል፡፡ ቅንጅት እንዳለው፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከአስተዳደራዊ ደንብ ውጭ የሆኑ ገደቦችን ተጠቅሞ ለመስከረም 22 ያቀደውን ሕዝባዊ ስብሰባ እንዳያካሄድ ከልክሎታል፡፡ ታህሣሥ 12 ቀን በቅንጅት ላይ ክሶች ከቀረቡ በኋላ ፓርቲው መሰብሰብ ተከልክሏል፡፡

በዓመቱ ውስጥ ደጋፊዎቻቸው የገሸቦው ፓርቲ ደጋፊዎች ያዘወተረና የተቀነባበረ ጥቃት ኢላማ እንደነበሩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይፋ አድርገዋል (ክፍል 1.ሐ.፣ 1.መ. እና 3 ይመልከቱ)፡፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)፣ የአዲስ አበባን ጨምሮ፣ የክልል መንግሥታት፣ ሰላማዊ የመሰብሰብና የመደራጀት መብትን መጋፋታቸውን ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ ለመስከረም 14 በአዲስ አበባ፣ ጐንደር፣ ባህር ዳር፣ አዋሳና ደሴ በቅንጅት የታቀዱ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ባለሥልጣኖች ሠርዘዋል፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ሊካሄዱ ኘሮግራም በተያዘባቸው የተለያዩ ከተሞች፣ ፖሊስ በርካታ የቅንጅት አባላትን በጀብደኛነት አስሯል፡፡ አብዛኞቹ ከአያሌ ቀናት እስራት በኋላ ተፈተዋል፡፡

የኦሮሞ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) በኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ድርጅት (ኦሕዴድ) ካድሬዎች፣ የደጋፊዎቹን የአባልነት መታወቂያ ካርዶች መቀማትና ተቀደው መጣል፣ ፖለቲካዊ ስብሰባዎቹ መጨናገፋቸውን፣ አባላቱ በፖሊስ ጣቢያዎችና በመከላከያ ሠራዊት ሰፈሮች መታሰራቸውን ዘግቧል፡፡ በማናሲቡ ወረዳ የመንግሥት አካላት ከበደ ጃቶንና ሌሎች የኦፌዴን (OFDM) አባላትን ይዘው በመከላከያ ሠራዊት ሰፈር ለጥቂት ቀናት አስረዋቸዋል፡፡ ጳጉሜ 4 ቀን በደንቢዶሎ የተከሰተውን ጠብ ተከትሎ፣ አንድ የኦሕዴድ (OPDO) ካድሬ የኦፌዴን አባል የነበረውን በየነ ዓለሙን መሣሪያ ተኩሶ ገድቶታል፡፡

የኦሮሚያ ርዕሰ ከተማ ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ መዛወሩን በመቃወም በጥር 1996 ሰልፍ የወጡትን በደበደቡና በመቶዎች የሚቆጠሩ ተቃዋሚ ተማሪዎች በባዶ እግራቸው በኮረት ላይ ለሰዓታት እንዲሮጡ እና እንዲንበረከኩ ባደረጉ ፖሊሶች ላይ ምንም እርምጃ አልተወሰደም:: በ1995 ወይም በ1994 ሰላማዊ ሰልፍ አድራጊዎችን በኃይል የበተኑ የፀጥታ ኃይሎችን በተመለከተም ሁኔታው የተለየ አልነበረም:: ዓመቱ ሲያልቅ፣ ያልተፈቀደ ስብሰባ በማድረጋቸው ቀደም ባሉት ዓመታት የታሰሩ ሰዎች እንደታሰሩ ስለመገኘታቸው በዓመቱ መጨረሻ የታወቀ ነገር አልነበረም::

በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት፣ በጠቅላላውም በሕዝብ ላይ፣ በተለይ ደግሞ የግንቦቱን ምርጫ ውጤት በመቃወም ሰልፍ በወጡ ላይ በፖሊስ፣ በጦር ሠራዊቱ እና በሚሊሺያዎች የተፈጸሙ ጥቃቶች በዓመቱ ውስጥ በእጅጉ ጨምረዋል:: ከሚያዝያ 28 እስከ ግንቦት 1 በአዲስ አበባ በተካሄዱ ሰልፎች ፖሊስን ከተጋፈጡ የከተማዋ ኗሪዎች መካከል 35 በጥይት ክፉኛ ቆስለው ወደ ሆስፒታሎች መግባታቸውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ዘግቧል:: በዓመቱ መጨረሻ መንግሥት እነዚህን ጥቃቶች በመመርመር አላጣራም::

የግንቦት 7 የምክር ቤት ምርጫዎችን ተከትሎ፣ ፖሊስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችን መከታተሉን፣ ማዋከቡንና ማሰሩን ቅንጅት እና ሕብረት ዘግበዋል:: ለምሳሌ፣ የቅንጅት ሊቀመንበር ኃይሉ ሻውልንና ቃል አቀባዩን ልደቱ አያሌውን ጨምሮ፣ ከሰው ጋር እንዳይገናኙ በመከልከል፣ የፀጥታ ኃይሎች የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን በቁም እስር አግተዋቸው ነበር:: መስከረም 6 ቀን 1998፣ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች የቅንጅትን ከፍተኛ አመራር አባል ደበበ እሸቱን ክፉኛ ደብድበውታል፤ ክስተቱን ፖሊስ አልመረመረውም:: ጥቅምትን በሙሉ፣ ለአዲስ አበባ ከንቲባነት የተመረጡትና የቅንጅት የምርጫ ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበሩትን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋንና የሕብረት ሊቀመንበር ዶ/ር መራራ ጉዲናን ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ይከታተሏቸውና ያዋክቧቸው ነበር::

በመስከረምና ጥቅምት፣ በአገሪቱ በሙሉ በርካታ እስራቶች ሲፈጸሙ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጽ/ቤቶች በኃይል ሲዘጉ እንደነበረ ሕብረት፣ ቅንጅት እና የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ) ዘግበዋል (ክፍል 1.መን ይመልክቱ)::

መስከረም 21 ቀን ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች፣ የቅንጅትን ቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት ብርቱካን ሚደግሳንና ዋና ፀሐፊውን ሙሉነህ ኢዮኤልን ማገታቸውንና መደብደባቸውን ቅንጅት አስታውቋል:: ሙሉነህ በቦርሳው ይዟቸው የነበሩ ሰነዶችን አጥቂዎቹ ወስደውበታል::

በ1996 ዓ.ም. ስለተፈጸመው የሜጫና ቱሉማ ማህበር (ሜቱማ) መታገድና ስለአባላቱ መታሰር ምንም አዲስ ነገር አልነበረም፡፡ አንዳንዶቹ የተያዙት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይመስላል፤ ከዚህም በላይ፣ ተጠርጣሪዎቹ እንዲለቀቁ ፍ/ቤት ቢያዝም፣ ጥቂቶቹ እንደታሰሩ ቆይተዋል (ክፍል 1.መን ይመልከቱ)፡፡

የመደራጀት ነፃነት

ምንም እንኳ ሕጉ የመደራጀት ነፃነትንና ያልተገደበ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ቢፈቅድም፣ በተግባር መንግሥት ይህን መብት ወስኖታል፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (መያድ) የሚመለከቱ አንዳንድ የፖሊሲ ጉዳዮች እልባት ሳያገኙ በመቀጠላቸው፣ መያዶች ሀብታቸውን ለማሰባሰብ የሚያስችሏቸውን ይፋ የሆኑ የቅንጅት መረቦች በመፍጠር መብታቸውን ነፍጓል፡፡ የፍትሕ ሚኒስቴር መያዶችን ይመዘግባል፣ ፈቃድም ይሰጣል፤ ይህን በተመለከተ በሂደቱ የግልጽነት መሻሻል ነበረ፡፡ ሆኖም፣ መንግሥት የሰብአዊ መብቶች ሊግን (Human Rights League) ለመመዝገብ እምቢ በማለቱ ገፍቶበታል (ክፍል 4ን ይመልከቱ)፡፡

በሕግ እንደተደነገገው፣ መንግሥት የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (ብምቦ) እንዲመዘገቡ ያስገድዳል፡፡ የቅንጅትን መዋሀድ ውድቅ በማድረጉ፣ ከምርጫው በኋላ ለቅንጅት እውቅና ለመስጠት ፈቃኛ ባለመሆኑ እና በአንፃሩ ደግሞ አወዛጋቢ ለሆነው ለአብኮ የአመራር ለውጥ እውቅና መስጠቱን ጨምሮ፣ እነዚህን የመሳሰሉትን የተቃዋሚ ፓርቲዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴን የሚወስኑ እርምጃዎችን በመውሰዱ፣ የብምቦ ነፃነት ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡

ሐ. የእምነት ነፃነት

ሕጉ ለሃይማኖት ነፃነት እውቅና ይሰጣል፤ በአጠቃላይ ሲታይ መንግሥትም ይህን መብት በተግባር ያከብራል፤ ይሁን እንጂ የአካባቢ ባለሥልጣኖች ይህን መብት አልፎ አልፎ ተጋፍተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና እስላም ዋናዎቹ ሃይማኖች ናቸው፡፡ ወደ 90 ከመቶ የሚሆነው ያገሪቱ ሕዝብ የአንዱ ወይም የሌላው ሃይማኖት አማኝ ነው፡፡

የሃይማኖት ተቋማት በፍትሕ ሚኒስቴር በየዓመቱ እንዲመዘገቡ መንግሥት ቢያስገድድም፣ ላለመመዝገብ በመረጡ ተቋማት ላይ መንግሥት እርምጃ ስለመወሰዱ ምንም የተዘገበ ነገር አልነበረም፡፡ ባለው ሕግ መሠረት፣ ማንኛውንም የልማት

ተግባር የሚያከናውን የሃይማኖት ድርጅት የልማት ክፍሉን ለብቻው እንደ መያድ ማስመዝገብ አለበት፡፡ የሃይማኖት ድርጅቶች ከልማት ክፍሎች ጋር ለተያያዙት ካልሆነ በስተቀር፣ ለውጭ የሃይማኖት ሠራተኞች መንግሥት የሥራ ፈቃድ አልሰጠም፡፡

በዓመቱ መጨረሻ በመንግሥቱ ኃይለማርያም (የደርግ) ዘመን የተወረሱ አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት ንብረቶች አልተመለሱም ነበር፡፡

ሕብረተሰባዊ በደሎችና አድልዎ

ለሃይማኖታዊ ተግባር ቦታ በማደላደል ረገድ መንግሥት አድልዎ እንዳደረገ የአናሳ ማህበረሰቦች የሃይማኖት ቡድኖች ዘግበዋል፡፡ ባለሥልጣኖች አንድ የኦሮሞ ባህላዊ ሃይማኖት ቡድንን አግደዋል፤ የሰጡትም ምክንያት የቡድኑ መሪዎች ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) እና ከሜጫና ቱለማ ማህበር (ሜቱማ) መሪዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው የሚል ነበር፡፡ ለቤተክርስቲያን መሥሪያና ለመቃብር ቦታ ሲፈልጉ የአካባቢ ባለሥልጣኖች አድልዎ እንደሚያደርጉባቸው የኘሮቴስታንት ቡድኖች አልፎ አልፎ አመልክተዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ (ኢእጉከጉ) ጋር ሲወዳደሩ፣ በባለሥልጣኖች እንደ "አዲስ መጤዎች" መታየታቸው የመሬት ድልድልን በተመለከተ እንደጐዳቸው የኘሮቴስታንት መሪዎች ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ (ኢእጉከጉ) ከመንግሥት መሬት በማግኘ ት ረገድ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን (ከኢኦቤ) የበለጠ ችግር እንደገጠመው ዘግቧል፡፡ ሌሎች ደግሞ መንግሥት ለኢእጉከጉ ያደላል ብለው ያምናሉ፡፡ ከከተማዋ አስተዳደር ፈቃድ ሳያገኙ በሰፋሪዎች የተገነቡ መስጊዶችን ለማፍረስ ባለሥልጣኖች ዒላማ አድርገዋቸዋል፡፡

የተዘገቡ ፀረ-አይሁድ (Anti-Semetic) ክስተቶች አልነበረም፡፡

(ለዝርዝር መግለጫ የ1997 ዓለምአቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርትን ይመልከቱ)፡፡

መ. በአገር ውስጥ የመንቀሳቀስ፣ የጉዞ፣ ወደሌላ አገር የመፍለስ እና ወደ አገር የመመለስ ነፃነት

ምንም እንኳ ሕጉ እነዚህን መብቶች ቢፈቅድም፣ መንግሥት በተግባር አንዳንዶቹን ገድቧል፡፡

በክልሉ ለሚዘዋወሩ ደህንነት ነው በማለት፣ መንግሥት ዓመቱን በሙሉ በጋምቤላ ክልል የዕርዳታ አቅርቦት መተላለፍንና በበጐ አድራጊ ድርጅቶች እጅ መግባትን ተከታትሏል፣ አንዳንድ ጊዜም ተቆጣጥሯል፡፡

ከአገር ማባረር በሕግ የተከለከለ ነው፤ መንግሥትም ማንንም ያገሪቱን ዜጋዎች በኃይል እንዲሰደዱ አላደረገም፡፡ ነገር ግን 54 ጋዜጠኞችን ጨምሮ፣ በርካታ ሰዎች በራሳቸው ተሰድደው በውጭ አገሮች ይገኙ ነበር (ክፍል 2.ሀን ይመልከቱ)፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ የቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ ኮሚቲ (ICRC) 427 ኢትዮጵያውያንን ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ፣ 192 ኤርትራውያንን ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ እንዲመለሱ አድርጓል፡፡ አብዛኞቹ ኤርትራውያንና ኤርትራዊ ግንድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን በመንግሥት ተመዝግበው መታወቂያ፣ የሆስፒታል እና ሌሎች የመንግሥት አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችሏቸውን በየስድስት ወሩ የሚታደስ የኗሪነት ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሆኖም፣ የአካባቢ መንግሥታዊ አካላት ለደሀ ኤርትራውያን የነፃ ህክምና አገልግሎት መብታቸውን ስለመንፈጋቸው በይፋ ያልተመዘገቡ ዘገባዎች ነበሩ፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR)፣ 556 ኢትዮጵያውያን በሶስተኛ አገሮች ማቋቋሙን ገልጾ ዓመቱ ከመገባደዱ በፊት ይህ ቁጥር ወደ 600 ከፍ እንደሚል ጠብቆ ነበር፡፡

በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች

ከ1996–1998 ከኤርትራ ጋር የተካሄደው ጦርነት በግምት 350,000 ሰዎችን አፈናቅሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በጐ አድራጊ ድርጅቶች ወደ 225,000 የሚገመቱትን መልሰው አቋቁመዋል፡፡ በግንቦት፣ የኖርዌይ ዓለም አቀፍ በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች (IDP) ፕሮጀክት የስደተኞች ምክር ቤት (Norwegian Refugee Council's Global IDP Project) በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን (አየሰ) ቁጥር በ151 እና በ167 ሺሕ መካከል አስቀምጦታል፡፡ ይህም በግምት በትግራይ ክልል 60 ሺሕ፣ በጋምቤላ 50 ሺሕ፣ በሱማሌ 10 ሺሕ እና በኦሮሚያ 20 ሺሕ ተፈናቃዮችን ያካትታል፡፡

በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል የተካሄዱ አስከፊ ግጭቶች በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አፈናቅለዋል፣ ሞትና የአካል ጉዳትም አስከትለዋል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)፡፡

የስደተኞች እንክብካቤ

ስለስደተኞች ይዞታ እአአ በ1951 በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት (1951 UN Convention) እና በዚሁ ስምምነት የ1967 ፕሮቶኮል መሠረት፣ የኢትዮጵያ ሕግ ጥገኝነት ወይም የስደተኝነት አቋም (refugee status) መስጠትን ይፈቅዳል፤ መንግሥትም የስደተኞች ደህንነት መጠበቂያ ሥርዓት አቋቁሟል፡፡ ብሔራዊ የስደት ሕግ በነሐሴ ወር 1996 ወጥቶ በዚያው ዓመት በግንቦት ወር ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በተግባርም መንግሥት ጥገኝነት ወይም የስደተኝነት አቋም በመስጠት፣ የስደተኞችን ያለፈቃዳቸው ጥቃት ይደርስብናል ብለው ወደሚፈሩበት፣ ወይም አምልጠው ወደ መጡበት፣ አገር መመለስን ተከላክሏል፡፡ በጠቅላላው ስደተኞችንና ተመላሽ ዜጐችን በመርዳት መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (ተመሰከኮ) እና ከሌሎች በጐ አድራጊ ድርጅቶች ጋር ተባብሯል፡፡ ከተመሰከኮ ጋር በመተባበር፣ ከሱዳን፣ ኤርትራና ሱማሊያ ለመጡ በ1951 ስምምነትና በ1967 ፕሮቶኮል መሠረት የስደተኛነት ቅድመ ሁኔታዎችን ለማያሟሉ ግለሰቦች መንግሥት ጊዜያዊ ጥበቃ ሰጥቷል፡፡

በ1996 መጨረሻ ከነበሩት 121 ሺሕ ስደተኞች ላይ፣ መስከረም ሲገባ ቁጥሩ ቀንሶ አገሪቱ በግምት 100,200 ስደተኞችን እያስተናገደች ነበር፡፡ የማህበራዊ አገልግሎቶች መስጫዎች ስለተሻሻሉ ስደተኞች በሚገኙባቸው ባለ 10 ሺሕ ሰዎችን ሊይዙ በሚችሉ ሰፈሮች በቂ የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃና የመጸዳጃ አገልግሎቶች አግኝተዋል፡፡ ዓመቱን ሙሉ ያልተቋረጠ በአማካይ በወር ከ200 እስከ 450 የሚደርስ የኤርትራውያን ፍልሰት ነበረ፡፡ ይህን ለመቋቋም መንግሥትና ተመሰከኮ (UNHCR) ለስደተኞች አዲስ ሰፈር በመፈለግ አብረው ሠርተዋል፡፡

በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በጋምቤላ ክልል በብሔረሰብ ልዩነት መነሻ ከደቡብ ሱዳን የመጡ 28 የኑዌር ስደተኞችን ገድለዋል የተባሉ ሦስት ሰዎችን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እስከ 14 ዓመት በሚደርስ እስራት መቅጣቱን በሚያዝያ ወር ዘግቧል፡፡

በዓመቱ መጨረሻ፣ በግምት 32 ሺሕ የኑዌርና ዲንካ ስደተኞች በጋምቤላ–ፉኒዶ ሰፈር ነበሩ፡፡

በተለያዩ ብሔረሰብ ቡድኖች መካከል በጋምቤላ የነበረው ብጥብጥ፣ ተመሰከኮ (UNHCR) ስደተኞችን ለመንከባከብ የሚያደርጋቸውን ጥረቶች አስቸጋሪ አድርጓቸዋል

(ክፍል 5ን ይመልከቱ)፡፡ በምዕራቡ የሃገሪቱ ክፍል ቀውስ የነበረ ቢሆንም፣ ለስደተኞች የሚቀርበው ምግብ ሳይቋረጥ ቀጥሏል፡፡ ሆኖም፣ በጐ አድራጊ ድርጅቶች እንደልብ መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው አንዳንድ ጊዜ የምግብ አቅርቦቶቹ ለተጠቃሚዎቹ መድረሳቸውን በበቂ ሁኔታ ለመከታተል አልቻሉም፡፡

ክፍል 3 የፖለቲካ መብቶች አከባበር፣ የዜጐች መንግሥታቸውን የመለወጥ መብት

ዜጐች መንግሥታቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲለውጡ ሕጉ ስለሚፈቅድላቸው፣ አንድ ሰው አንድ ድምፅ በሚለው መርህ መሠረት በተካሄዱና በአጠቃላይ ነፃና ፍትሃዊ በነበሩ ምርጫዎች ዜጐች በመብታቸው ተጠቅመዋል፡፡ ሆኖም፣ መዛባቶች፣ የመራጮችና የምርጫ ታዛቢዎችን ማስፈራራት፣ በብዙ ቦታ ድምፅ አሰጣጡን አበላሽተውታል፡፡ በተግባርም ገዢው ፓርቲ ኢሕአደግ መንግሥቱን ተቆጣጠሮታል፡፡

የመንግሥት የጐሳ ፌዴራላዊ ሥርዓት ፖሊሲ የተፈለገውን ተናጠል ውክልና ያላቸውን ክልሎች ስለፈጠረ ትላልቆቹ የጐሳ ቡድኖች በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መወከላቸውን አረጋግጧል፡፡ ይሁንና አናሳ ብሔረሰቦች በም/ቤቱ ውክልና አጥተዋል፡፡ በቂ የሕዝብ ብዛት ስለሌላቸው፣ የውክልና መቀመጫ ያላገኙ 23 የጐሳ ቡድኖች በ6 ክልሎች ነበሩ፡፡ ሆኖም፣ በግንቦቱ ምርጫ የእነዚህ ማህበረሰቦች አባላት የነበሩ ግለሰቦች ከ547 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መቀመጫዎች ለ23ቱ ተወዳድረዋል፡፡

ምርጫዎች እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ

በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች አስተያየት መሠረት፣ ከ547 መቀመጫዎች ውስጥ የኢሕአዴግ ጥምረት 372 ያሸነፈባቸው፣ የግንቦት ብሔራዊ ምርጫዎች በአጠቃላይ የሚታመኑ ነበሩ፡፡ ውክልናቸውን ከ12 መቀመጫዎች ወደ 172 ከፍ በማድረግ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያልተጠበቀ ውጤት አሳይተዋል፡፡ መራጮችንና የምርጫ ታዛቢዎችን ማዋከብን ጨምሮ የተከሰቱት መዛባቶች በብዙ ቦታ ድምፅ አሰጣጡን ጥላሸት ቀብተውታል፡፡ ከምርጫ ቦርድ ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት/ኢሕአዴግ "የመጨረሻ" ያለውን የምርጫ ውጤት አሳውቋል፡፡ አንዳንድ ታዛቢዎች፣ ግድያዎች፣ የሰዎች መሰወር፣ የመራጮች ማስፈራራትና ማዋከብ እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች መታሰር በተለይ በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች እንደነበሩ ዘግበዋል (ክፍል 1.4.፣ ለ. እና መ. ይመልከቱ)፡፡ ያም ሆኖ፣

የካርተር ማዕከልን ጨምሮ፣ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች፣ የግንቦቱን ምርጫዎች ዲሞክራሲን ለማምጣት አገሪቱ በምታደርጋቸው ጥረቶች ዋነኛ ዕድገት አሳይተዋል ሲሉ አወድሰዋል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ የገዥው ፓርቲ መሣሪያ ነው በማለት ከሰዋል፤ ትርፍ የምርጫ ካርድ በገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች በድምፅ መስጫ ሳጥን መታጨቅን፣ የተጭበረበረ የድምፅ ቆጠራ፣ ጉቦ፣ ግድያዎችን፣ ድብደባዎችን፣ ሰፊ ማስፈራራትና ማዋከብን ጭምሮ፣ የምርጫ መዛባቶች ስለመፈጸማቸው ሲነገረው፣ ቦርዱ እርምጃ አልወሰደም ሲሉ ተቃዋሚዎች ከሰውታል፡፡ የብሔራዊውን ምርጫ ውጤቶች በመቃወም፣ ቅንጅት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መቀመጫ መያዝን ተቃውሟል፡፡

ግንቦት 12 መንግሥት የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ድምፅ አሰጣጡ በትክክል ባልተካሄደባቸው በርካታ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የፓርላማ ምርጫዎች ግንቦት 14 እንደገና እንደሚካሄዱ ባስታወቀው መሠረት፣ ነሐሴ 15 ምርጫዎች ተካሄደዋል፡፡

የምርጫውን ውጤቶች በመቃወም፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በማማረር ማመልከቱንና፣ የ150 የምርጫ ክልሎች ውጤቶችን አለመቀበሉን ቅንጅት ግንቦት 23 ቀን አስታወቀ፡፡ ስለተዛቡ የድምፅ ቆጠራዎች ምዝገባ በነበሩ ዘገባዎች የተነሳ ስጋት እንደገባው የካርተር ማዕከል ባወጣው መግለጫ "የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ያለአግባብ ስለመወሰዳቸው እና በሚገባ ስላለመጠበቃቸው ታዛቢ ቡድኖቹ መረጃ እንደነበራቸው ገልጿል"፡፡ ማዕከሉ በተጨማሪም "በምርጫው ቀንና ከምርጫው በኋላ ማስፈራራትና ማዋከብ እንደነበረ" ዘግቧል፡፡

ቁልፍ በሆኑ አካባቢዎች መዛባቶችን በመጥቀስ፣ የግንቦት 7 ምርጫዎች "ዓለምአቀፍ መስፈርቶችን አላሟሉም" በማለት የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ተልዕኮ (አሕምታተ-EUEOM) ኃላፊ እና የሕብረቱ ፓርላማ አባል አና ጐሜዝ (Anna Gomes) የመጀመሪያ ሪፖርታቸውን አወጡ፡፡ በምላሹ የማስታወቂያ ሚኒስትሩና ሌሎች የመንግሥት ሹማምንት አሕምታተን (EUEOM) በይፋ በማውገዝ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ እና በምሥጢር፣ መሠረት የሌለው መረጃ ለተቃዋሚዎች አድርሷል ሲሉ ከሰውታል፡፡

የአውሮጳ ህብረት ባወጣው መግለጫ "የሰብአዊ መብት መከበርንና ሚዛናዊ የሚዲያ አጠቃቀምን ጨምሮ በአሳሳቢ ደረጃ እንደሚገኙ ገልጾ፣" ዲሞክራሲን በማምጣቱ ሂደት፣ "ምርጫዎቹ እንደ አንድ ዋነኛና ትልቅ እርምጃ" አድርገው እንደሚያቸው አሕ (EU) ገልጿል፡፡

በገዥው ፓርቲና በዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በተደረጉ ድርድሮች፣ መፍትሔ ላላገኙ ከምርጫው ጋር የተያያዙ በርካታ አቤቱታዎች እልባት የሚሰጥ ገዜያዊ የአቤቱታዎች አጣሪ ሂደት በሁለቱ ወገኖች ሰኔ 3 ስምምነት ተፈረመ፡፡ የካርተር ማዕከል እንዳሳወቀው፣ በአገሪቱ ዙሪያ የተለያዩ 44 አቤቱታ አጣሪ ቡድኖች (panels) በ178 የምርጫ ክልሎች ይፋ የማጣራትና አቤቱታ የማዳመጥ ሂደቶች አካሄደው፣ ውጤቱም በ31 የምርጫ ክልሎች አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ብምቦ (NEB) የወሰነበት ነበር፡፡

በሱማሌ ክልል ለነሐሴ 15 በተቀጠሩት የምክር ቤት ምርጫዎች ዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደማይሳተፉ ነሐሴ 10 ዓለምአቀፋዊ የዜና አውታሮች ዘገቡ፡፡ በዚህም የተነሳ፣ በሥልጣን ላይ የነበረው የሱማሌ ሕዝብ ዲሞክራቲክ ፓርቲ 23ቱንም የፌዴራል ም/ቤት መቀመጫዎች አሸነፈ፡፡ የክልሉን ምርጫ የማይናቁ መዛባቶች እንዳበላሹት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢያመለክቱም፣ ብምቦ (NEB)፣ ክሶቹን ገምግሞ እንዳልተቀበላቸው አስታውቋል፡፡

ተቃዋሚዎች በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መሳተፋቸውን በተመለከተ፣ መንግሥት እና የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች በጥቅምት ወር ተወያይተዋል፡፡ በርካታ የሕብረቱ (UEPF) አባላት፣ በም/ቤቱ ቦታቸውን ለመያዝ ሲወስኑ፣ የቅንጅት (CUD) የፓርላማ አዲስ ተመራጭ አባላት ግን የግንቦቱን ምርጫ ውጤት በመቃወም በፓርላማው መክፈቻ እንደማይገኙ አስታውቀዋል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ አብዛኛዎቹ የቅንጅት አባላት ፓርላማ ገብተዋል፡፡ ከዚያም የመኪና ጥሩንባ ማጮህን፣ የኢሕአዴግ ከሆኑ የንግድ ድርጅቶች ጋር አለመገበያየትን (boycot) እና የመንግሥት ደጋፊዎች ናቸው የተባሉ ግለሰቦችን ማግለልን የመሳሰሉ የሰላማዊ እምቢተኛነት (civil disobedience) እርምጃዎች እንዲወሰዱ ቅንጅት ጥሪ አደረገ፡፡ መንግሥት የቅንጅትን ጥሪ ሕገ ወጥ ነው ሲል በይፋ አስታወቀ፡፡

ከጥቅምት 22 ቀን ጀምሮ፣ በተቃዋሚዎች የተጠሩ በሁከት የታጀቡ ፀረ-መንግሥት ተቃውሞዎች በአዲስ አበባ ተካሄዱ፡፡ መንግሥትም ሕገ ወጥ በሆኑ እንቅስቅሴዎች ተሳትፋችኋል በማለት፣ በአያሌ ደርዘን የሚቆጠሩ መሪዎችንና እንዲሁም የነዓው

ኘሬስና የሲቭል ማህበረሰብ ቡድኖች አባላትን ያዙ፡፡ የፀጥታ ኃይሎች፣ ለሰልፍ ከወጡት ከ14 ሺሕ በላይ የሚሆኑትን ሰዎች ያለምንም ክስ ይዘው አሰሩ፡፡ የመከላከያ ሠራዊቱ ጣልቃ መግባት፣ በጀብደኝነት ማሠርን እና መግደልን ጨምሮ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች መጣስን አስከተለ፡፡ የፓርቲውን ኘሬዝዳንት ኃይሉ ሻውልን፣ ተቀዳሚ ምክትል ኘሬዝዳንቷን ብርቱካን ሚደግሳን፣ ዋና ጸሐፊውን ሙሉነህ ኢዮኤልን እና የአዲስ አበባ ዕጩ ተመራጭ ከንቲባ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ ከቅንጅት 20 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ቢያንስ 12 የሚሆኑትን የፀጥታ ኃይሎች ያዙ፡፡ ከቀረቡባቸው ክሶች መካከልም የአገር ክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ይገኙበታል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ሰዎቹ በእስራት ሆነው ፍ/ቤት መቅረባቸው ተጀምሮ ነበር፡፡

ኢሕአዴግ፣ ተባባሪዎቹ እና ደጋፊዎቹ በክልል መንግሥታትና በፌዴራሉ መንግሥት የሚሰየሙበትን 108 አባላት ያሉትን የፌዴሬሽን ም/ቤት መቀመጫዎች በሙሉ ተቆጣጠረዋል፡፡ የኢሕአዴግ አባልነት ለአባላቱ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ለምሳሌ፣ ፓርቲው በርካታ የንግድ ድርጅቶች ስላሉት ለታማኝ ደጋፊዎቹ ሥራ ይሰጣል፡፡ ከመንግሥት በተጨማሪ፣ የሬዲዮ ጣቢያ ለማካሄድ ፈቃድ የተሰጣቸው የትግራይ ሕዝብ አርነት ግንባር (TPLF) አባላት ነበሩ (ክፍል 1.ሀን ይመልከቱ)፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ ትላልቅ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የጥምረት ድርድር አድርገዋል፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ (AEUP)፣ ቀስተደመና ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ-መድኅን፣ እና የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሊግ በአንድነት፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲን (CUD) መሠረቱ፡፡ ይህም ቅንጅትን በአገሪቱ ከሁሉም በበለጠ ጠንካራው ተቃዋሚ የፖለቲካ ጥምረት አድርጐታል፡፡ በዓመቱ ውስጥ ሌሎች ተቃዋሚዎች፣ በግንቦቱ ብሔራዊ ምርጫዎች፣ በፌዴራል ም/ቤት 11 መቀመጫዎች ያገኘውን የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራቲክ ንቅናቄን (ኦፌዴን-OFDM) መሠረቱ፡፡ የአካባቢ ቢሮዎችን ለመክፈት፣ በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው፡፡ እንደ ቅንጅት፣ ሕብረትና ኦፌዴን ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳሉት በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት አንፃር በአካባቢ ባለሥልጣኖች ማስፈራራትና ጥቃት ገጽታውን ሳይለወጥ ዓመቱን ሙሉ ቀጥሏል፡፡

ግድያን፣ ድብደባን፣ ቤት ማቃጠልንና የንብረት መዝረፍን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ እነዚህን የመሰሉ ሁኔታዎች መከሰታቸውን የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ነፃ ጋዜጦች ዘግበዋል፡፡ በእነዚህ በበርካታዎቹ የተዘገቡ ክስተቶች፣ ሰዎች ማዳበሪያ እና ሌሎች የግብርና አገልግሎቶችን፣ የጤና እንክብካቤን ወይም ሌሎች በመንግሥት

ቁጥጥር የሆኑ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ከፈለጉ እንደተባለው የተቃዋሚ ፓርቲ አባልነታቸውን መሠረዝ እንዳለባቸው በባለሥልጣኖች ተነግሯቸዋል፡፡

በ1995 መጨረሻ እና በ1996 መጀመሪያ ላይ፣ የኮንሶ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሕብረትን (ኮሕዲሕ-KPDU)፣ እና በኮሕዲሕ ቁጥጥር ስር በነበረው አባሮባና ጃርሶ የአካባቢ ም/ቤቶችን በኢሕአዲግ መበተንን በተመለከተ ወይም የኮሕዲሕ አባላትን እስራትና ድብደባ አስመልክቶ አዲስ ነገር አልነበረም፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አባል በቀለ ታደሰ በየካቲት ወር 1996፣ በድንጋይ መደብደብም ሆነ ወይም በመጋቢት የአንኮበር ወረዳ የፓርቲው አደራጅ ሊቀመንበር የዘመድኩን ገብረ ኪዳንን ቤት በቦምብ መቃጠልን በተመለከተ ባለሥልጣኖች በተጠያቂዎች ላይ ምንም እርምጃ አልወሰዱም፡፡

ከ19ኙ የሚኒስትሮች ም/ቤት አባላት መካከል ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ፣ ሌሎች ሴቶችም በከፍተኛ የሥራ ቦታ ላይ ተመድበው ነበር፡፡ 547 መቀመጫ ባለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 116 ሴቶች ሲገኙ፣ 113 አባላት ባሉት የፌዴሬሽን ም/ቤት ደግሞ 21 ነበሩ፡፡ ከ14 የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች 3ቱ ሴቶች ነበሩ፡፡ በግንቦቱ ምርጫዎች ወቅት፣ ከሕዝብ ታዛቢዎች፣ ከፓርቲ ሠራተኞችና ከምርጫ ጣቢያዎች ሹማምንት መካከል ከግማሽ በላይ ሴቶች ነበሩ፡፡

የመንግሥት ሙስኛነት እና ግልጽነት

ሙስናን በመዋጋት የፍትሕ ሚኒስቴር ቅድሚያ ኃላፊነት አለበት፡፡ ማህበረሰብዓዊ ጫና፣ ባህላዊ ልማዶችና የሕግ ገደቦች ሙስናን ወስነውታል፡፡ ያም ሲሆኖ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን፣ የኃይል ማመንጫ እና የሌሎች መሠረተ ልማቶች ጨረታዎችን በመሰረዙ ሂደት ግልጽነት ባለመኖሩ፣ የሙስና ጥርጣሬዎችን አስነስቷል፡፡ በተጨማሪም በመንግሥትና በፓርቲ ለተያዙ የንግድ ድርጅቶች አድሎአዊ የመሬት ሊዝና ብድር መስጠታቸው ሲታይ፣ የመንግሥት ባልሥልጣኖች የመንግሥት የልማት ተቋማትን ወደ ግል የማዘወሩን ሂደት የቆለመሙ ይመስል ነበር፡፡

ሕጉ ዜጐች የመንግሥት መረጃን ማግኘት እንደሚገባቸው ደንግጓል፣ በተግባር ግን ይኸ በአብዛኛው ተገድቧል፡፡

መንግሥት የሚያወጣቸውን ሕጐችና ደንቦች ተግባራዊ ከመሆናቸው አስቀድሞ በብሔራዊ ነጋሪት ጋዜጣ ያሳትማል፡፡ የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ በመንግሥት

በኘሬስና በሕዝብ መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይመራል፡፡ ሆኖም፣ ከግሉ ኘሬስ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት መንግሥት አዘውትሮ እምቢ ብሏል (ክፍል 2.ሀን ይመልከቱ)፡፡

ክፍል 4 ተደረጉ የተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትን በሚመለከት ዓለምአቀፋዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ወገኖች ስላደረጉት ምርመራ የመንግሥት አመለካከት

የተወሰነ የመንግሥት ገደብ ቢኖርባቸውም፣ በአጠቃላይ ያገር ውስጥ እና ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድኖች፣ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን በመመርመር እና ግኝታቸውን በማተም ተንቀሳቅሰዋል፡፡ በአጠቃላይ መንግሥት ባገር ውስጦቹ ላይ፣ እንዲሁም በአንዳንድ ዓለምአቀፋዊ ታዛቢዎች ላይ ጥርጣሬ እና ስጋት ነበረው፡፡ ከህዳር የተቃውሞ ክስተቶች በኋላ፣ መንግሥት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድኖችን የማጐሪያ ማዕከሎችን ከመጐብኘት ወይም በእነዚሁ ቦታዎች የነበረውን ሁኔታ ከመመርመር አግዷቸዋል፡፡ ጽ/ቤቶቻቸው በውጭ አገር የሆኑና ከምርጫ ጋር የተያያዘ ሥራ በመሥራት ላይ የነበሩ ሁለት/ሶስት መያዶችን (NGOs) በሚያዝያ ወር ከአገር አባሯል፡፡ ባለሥልጣኖች በወገናዊነት ከከሰሱት በኋላ፣ የግንቦቱን ምርጫ በመከታተል የነበረው ከፍተኛ የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢ ስግረድ ፖውስዋንግ (Siegried Pausewang) ሥራውን አቋርጧል፡፡

ሁለቱ በኢትዮጵያ በጣም የታወቁት ያገር ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (EHRC) እና የኢትዮጵያ ሴቶች የሕግ ባለሞያዎች ማህበር (EWLA) ናቸው፡፡ መንግሥት የኢሰመጉን ሪፖርቶች አዘውትሮ ከማቃለሉም በተጨማሪ ድርጅቱን የፖለቲካ ድርጅት ነው ይለዋል፡፡

የኢሴሕባማ (EWLA) ዋና ተግባር በሕግ ነክ ጉዳዮች ሴቶችን መወከል ነው፡፡ እነዚህና ሌሎች ቡድኖች በዋናነት የሚያካሂዱት ስለሰብአዊና ሲቪክ መብቶች ትምህርት መስጠት፣ ሕጋዊ እገዛ ማድረግ እና የፍርድ ሂደቱን መከታተል ናቸው፡፡ ሆኖም፣ መንግሥት መረጃ ካለማካፈሉ በተጨማሪ፣ የአገር ውስጥ መያድ (NGO) ማህበረሰብ የሚያቀርቧቸውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አያምንም፡፡

ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (OLF) ጋር አለው ስለሚለው ትስስር፣ መንግሥት የሰብአዊ መብቶች ሊግን (Human Rights Leauge) መመርመሩን ቀጥሎበታል፡፡ የድርጅቱ ቢሮዎች እንደተዘጉ ከመቆየታቸውም በላይ፣ በ1989 ላስገባው የምዝገባ ጥያቄም

እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ መንግሥት ለድርጅቱ ምላሽ አልሰጠም፡፡ ይኸም ፍርድ ቤት ድርጅቱ እንዲመዘገብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከተባበሩት መንግሥታት እና ቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ ኮሚቲን ከመሳሰሉ ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች ጋር መንግሥት ተባብሯል፡፡ በዓመቱ ውስጥ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የተከሰተውን ሁከት ተከትሎ፣ የቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ ኮሚቴ እስር ቤቶችንና ሌሎች የማገቻ ሥፍራዎችን ለመጐብኘት መቻሉ ተገድቦ ነበር፡፡

በሕግ አስፈጻሚ አካላት የሚፈጸሙ የአስተዳደር በደሎችን በተመለከተ አቤቱታዎችን የመቀበልና የመመርመር ሥልጣን ያለው የእንባ ጠባቂ ቢሮ እና የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋምን ሕጉ ቢያዝም፤ በዓመቱ መጨረሻ ከሁለቱ አንዳቸውም ሙሉ በሙሉ አይሠሩም ነበር፡፡ ተቋማቱ የነበራቸው ሁለንተናዊ አቅም ውሱን ስለነበረ፤ ዓመቱ ሲገባደድ አንዳቸውም የሥራ ሪፖርት አላወጡም ነበር፡፡

የፍትሕ ሚኒስቴር ለዳኞች፣ ለአቃብያነ ሕግ፣ ለፖሊስና ለአካባቢ ማህበረሰቦች አባላት በአገሪቱ ዙሪያ የጀመረውን ሶስት ዓመት የሚዘልቅ የሥልጠና አውደ ጥናት ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ ሆኖም፣ ከምርጫው ጋር የተያያዘው ሁከት የፕሮግራሙን እንቅስቃሴዎች ክፉኛ አሰናክሏቸዋል፡፡

በ1995 መጨረሻ እና 1996 በብሔረሰቦች መካከል ከተከሰተው ብጥብጥ ጋር በተያያዘ፣ ምናልባት በመንግሥት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን አንድ የፓርላማ ኮሚሽን አጣርቷል፡፡ በመጋቢት፣ ሂውማን ራይትስ ወች (Human Rights Watch)፣ ኮሚሽኑ ከብጥብጡ ጋር በተያያዘ የሞቱ ሰዎችን ቁጥር በእጅጉ እንደሳነሰው በማስታወቅ፣ የጦር ሠራዊትም ሆነ የፌዴራል ፖሊስ ባለሥልጣኖች ሁከቱን ያነሳሱትን ወደ ፍ/ቤት ለማምጣት ምንም ዓይነት እርምጃ አልወሰዱም ሲል ተከራክሯል፡፡

ክፍል 5 አድልዎ፣ ማህበረሰባዊ በደሎች እና በሕገወጥነት በሰዎች መነገድ (Trafficking)

ሕጉ ዘርን፣ ቀለምን፣ ጾታን፣ ቋንቋን፣ የትውልድ አገርን፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አስተሳሰብን ወይም ሕብረተሰብአዊ አቋምን የተመረኮዘ አድልዎ ይከለክላል፡፡ ሆኖም፣ መንግሥት እነዚህን ክልከላዎች (probhibitions) በተግባር በውጤታማነት አላስከበራቸውም፡፡

ሴቶች

ባል በሚስት ላይ የሚፈጽመውን አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ፣ የቤተሰብ ሁከት የተንሰራፋ ሕብረተሰብአዊ ችግር ነበር፡፡

በሐምሌ የተደረገ የዓለም ባንክ ጥናት፣ ከገጠር ሴቶች 88 በመቶ እና ከከተማ ሴቶች ደግሞ 69 በመቶ የሚሆኑት ባሎቻቸው ሚስቶቻቸውን የመምታት መብት አላቸው ብለው ያስባሉ፡፡ ሴቶች ወደ ፖሊስና ፍ/ቤት መሄድ ቢችሉም፣ ሕብረተሰብአዊ ልማዶችና የሌሎች አስፈላጊ መሠረተ ልማት (infrastructure) ውሱንነት የሴቶችን፣ በተለይ የገጠሮቹን፣ ሕጋዊ ማረሚያን (legal redress) ከመሻት ከልክሏቸዋል፡፡ በተወሰነ ደረጃ መንግሥት አጥፊዎችን ወደ ፍርድ ቤት ማምጣት ጀምሯል፡፡

በጥቅምት ወር መንግሥት በሚኒስቴር ደረጃ የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ውስጥ ማቋቋሙን አስታውቋል፡፡

በሰኔ 1996 የጸደቀው አዲስ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል አድርጐታል፤ ነገር ግን በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረግ አስገድዶ መድፈር በግልጽ አይናገርም፡፡ ስለሕጉ ተፈላጊው የግንዛቤ ሥልጠናና የገንዘብ አቅርቦት አለመኖር የተነሳ መንግሥት ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ አላዋለውም፡፡ በዚህ ረገድ፣ ባህላዊ ልማዶች በተለይ በገጠር ዓይነተኛ መሰናክል እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ አገሪቱ ተስማሚ የላቦራቶሪ ተቋማትና የአስገድዶ መድፈር መሣሪያዎች (rape kits) ስለሌሏት፣ አስገድዶ መድፈርን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ተመሥርቶ መንግሥት የተወሰነ እርምጃ ወስዷል፡፡

ባህላዊ ልማዶች፣ አስገድዶ የመድፈር ክስተቶችን መመርመርና ወደ ፍትሕ ማቅረብን አደናቅፈውታል፡፡ ብዙ ሴቶችም በሕግ ስላሏቸው መብቶች ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ ይህም የክስተቶችን በሙሉ አለመመዝገብ አስከትሏል፡፡ በአዲስ አበባ በዓመት ቢያንስ አንድ ሺሕ የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶች እንደሚፈጸሙ ታዛቢዎች ተናግረዋል፡፡ ይፋ በተደረገ የፖሊስ ዘገባ የተመዘገቡት ግን በዓመት 400 ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡ ጋዜጦች የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶችን፣ በተለይም ለአቅመ ሄዋን ባልደረሱት ላይ፣ ጉዳት ያስከተሉትን በየጊዜው እየተከታተሉ ዘግበዋል፡፡ ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ አስገድዶ ደፋሪዎች ላይ ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት ፍ/ቤቶች ከ10 እስከ 15 ዓመት እስራት ፈርደዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሴቶች የሕግ ባለሞያዎች ማህበር (ኢሴሕባማ)፤ የተፈጸሙ የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶችን ቁጥርና የጥፋተኛነት ብይን የተሰጠባቸው ፋይሎች ቁጥር በተመለከተ በ1996 ዓ.ም. አንድ ጥናት ያካሄደ ቢሆንም፣ በዓመቱ መጨረሻ የጥናቱ ውጤት ይፋ አልተደረገም ነበር፡፡

ልማዱን ለማስቀረት መንግሥት ጥረት ያደረገ እና ድርጊቱም ሕገወጥ ቢሆንም፣ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለጋብቻ መጥለፍ፣ አማራን፣ ኦሮሚያንና ደቡብን ጨምሮ በአንዳንድ ክልሎች እንደተንሰራፋ ቀጥሏል፡፡ አብዛኞቹን የጠለፋ ጋብቻዎች፣ በግድ የሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነትን ከማስከተላቸውም በላይ በጠለፋው ብዙ ጊዜ ሴቶቹ በሰውነታቸው ላይ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ በሕግ የተደነገገው ዝቅተኛ የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት ቢሆንም፣ ብዙዎቹ የተጠለፉ ልጃገረዶች እስከ 7 ዓመት በሆነ ዝቅተኛ ዕድሜያቸው አግብተዋል፡፡ ጠለፋዎች በቤተሰቦች፣ በማህበረሰቦችና በብሔረሰቦች መካከል ግጭት አስነስተዋል፡፡ ባለሥልጣኖች ካልሰረዙት በስተቀር፣ ተጠላፊዋ ጠላፊዋን ለማግባት ፈቃደኛ ከሆነች፤ ጠላፊው ምንም ዓይነት ቅጣት አልተጣለበትም፡፡ ጠላፊው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ እንኳ፤ ተጠላፊዋ ስታገባው ባለሥልጣኖቹ ብይኑን ሽረውታል፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙትን ጥቃቶችና ያለ ዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ ስላሉት ችግሮች የሕብረተሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣቱን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች ነበሩ፡፡

አብዛኞቹ ሴት ልጆች አንዱ ወይም ሌላው ዓይነት ግርዛት (female genital mutilation-FGM) ይደረግላቸዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ እንደሚደረገው፣ በተወለዱ በሰባት ቀናቸው ጨቅላዎቹ ቂንጥራቸውን ይቆረጣሉ (clitoridectomy)፡፡ ይኸም የቂንጥር እና በከፊል የብልት ከንፈር መቁረጥን (excision) ያካትታል፡፡ ከሁሉም በላይ አደገኛ ው የግርዛት ዓይነት የብልታቸውን ከንፈር አሟጥጦ መቅፈፍ (infibulation) ለአቅመ ሄዋን በመድረሻቸው ወቅት ገጥሟቸዋል፡፡ በዓመቱ ውስጥ ይፋ በተደረገው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሥነ ሕዝብ እና ጤና ቅኝት (demographic and health survey) መሠረት፣ በመላ ሴቶች ዘንድ ግርዛት ከ80 ወደ 74 በመቶ፣ ሴቶች ለልማዱ ያላቸው ድጋፍ ደግሞ ከ60 ወደ 29 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በ1996 የወጣው አዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሴቶችን ግርዛት ከሶስት ዓመት ባላነሰ አስራትና ከብር 500 (USD 58) ያላነሰ መቀጫ የሚያስከትል ወንጀል አድርጐታል፡፡

እንደዚሁም አሰቃቂው የብልቶች ግርዛት (infibulation) ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል፡፡

መንግሥት ጐጂ የልማድ ግርዛትን (FGM) ጨርሶ ለማጥፋት ጥቂት እርምጃዎች ወስዷል፡፡ በት/ቤቶች በሚሰጥ ትምህርትና ሰፋ ባለ የመገናኛ ብዙሀን ዘመቻዎች ልማዱን ለማስተው ሠርቷል፡፡ በሐምሌ ወር 1996 በሐመር ወረዳ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ፣ አንድ የወረዳው መኰንን ሚስቱን ግርዛት (FGM) እንድታደርግ በማስገደዱ ምክንያት ከሥራ አባሮታል፡፡ በዚሁ ዓመት፣ የደቡብ ኦሞ ዞን የቅስቀሳና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ምክትል ኃላፊ፣ ጐጂ ባህላዊ ልማዶችን ለማጥፋት በ197 አካባቢዎች ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን አሳታውቀዋል፡፡ አሁንም በ1996፣ በአንድ ቀን ብቻ 62 ልጃገረዶችን ገርዘዋል የተባሉ አራት ሴቶችን የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ፖሊስ ይዞ አስሯል፡፡ ይህም የሆነው የግርዛትን ጐጂ ውጤቶች በተመለከተ የተካሄደ አንድ የሚዲያ ዘመቻን ተከትሎ የአካባቢው ኗሪዎች ባደረጉት ጥቆማ ነው ተብሏል፡፡

ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ሴቶች ሽርሙጥና (prostitution) በሕግ የተፈቀደ ቢሆንም፣ ችግርነቱ ቀጥሏል፡፡ ማቃጠርና ከሽርሙጥና ተጠቃሚ መሆን ሕገወጥ ነበሩ፡፡ በሽርሙጥና የሚበዘበዙ አበክረው የሚናገሩት ድህነት ዋና መንስኤ እንደሆነ ነበር፡፡

የኢሴሕባማ (EWLA) እና ዓለም አቀፍ የቦታ መቀየር ድርጅት (IOM) በኢንዱስትሪና የቤት ሠራተኛነት ወደ መካከለኛ ምሥራቅ የሚሄዱ የሴት ሠራተኞች ጥቃት እንደሚገጥማቸው ዘግበዋል (ክፍል 5 ላይ ማስተላለፍ-trafficking የሚለውን ይመልከቱ)፡፡

ወሲባዊ ማዋከብ ተንሰራፍቷል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አጥቂውን ከአንድ ዓመት ተኩል እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡ ሆኖም፣ ከዚህ ጋር የተያያዙ ሕጐች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አልተደረጉም፡፡

የሰዎችን ሁሉ እኩልነት ሕጉ ቢያውጅም፣ ድንጋጌዎቹን መንግሥት በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባራዊ አላደረጋቸውም፡፡ ሕጉ ለወንዶችም ለሴቶችም፣ የሕጋዊ የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት እንዲሆን ደንግጓል፤ ሲቪል ሕጉን ከባህላዊና ሃይማኖታዊ ሕግ በላይ አድርጐታል፤ ከአምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው የኖሩ ያልተጋቡ፤ ጥንዶች ንብረት እንዲካፈሉ ፈቅዷል፤ በፍ/ቤቶች ፈንታና ቦታ፣ ከጋብቻ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን የሚዳኙ የቤተሰብ ጉዳይ ሽምጋዮችን አስወገዷል፤ የተጋቢዎች የወል የቤተሰብ ሀብት እና ንብረትን በጋራ ማስተዳደርን ፈቅዷል፤ ፍች ወይም መለያየት ሲከሰት ፍ/ቤቶች ለልጆች ወይም ከሁሉም አቅመቢስ ለሆነ የቤተሰቡ አባል

ሁኔታን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ያስገድዳል፤ ፍች ወይም ሞትን ተከትሎ እንደገና ለማግባት ለሚፈልጉ ሴቶች፣ ስድስት ወር የመቆያ ጊዜ ሕጉ ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የክልል ም/ቤቶች የየአካባቢያቸውን የቤተሰብ ሕግ ለመወሰን ሥልጣን ነበራቸው፡፡ በዚህም መሠረት አራት ክልሎች የራሳቸውን የቤተሰብ አውጥተዋል፡፡ እነዚሁም አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያና አዲስ አበባ ናቸው፡፡ ከፌዴራል ይልቅ የክልል ሕጎች በዝርዝር ይዘታቸው ይበልጥ አካባቢ ጠቀስ ናቸው፡፡ የክልል ሕጎች በተመሳሳይ ሁኔታና ደረጃ ተግባራዊ አይደረጉም፤ በሕግ ከብሔራዊው ሕገ መንግሥት ጋር ሊጋጩ አይችሉም፡፡

በሴቶች ጉዳይ ላይ በሚንቀሳቀሱ ቡድኖች የማሳሰብ ቅስቀሳ፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኃላፊ የሴቶችን ለፓርላማ እጩ ተወዳዳሪነት ከሐምሌ 1996 በይፋ ደግፈዋል፡፡

ፀረ-ሴት አድልዎ፣ 85 ከመቶ የአገሪቱ ሕዝብ በሚኖርበት ገጠር እጅግ በጣም የከረረ ነበር፤ ሕጉ፣ ባልዮውን የቤተሰቡ ሕጋዊ የበላይ እንደሆነ ማወቅንና ከአምስት ዓመት በታች ላሉት ደግሞ ብቸኛው ጠባቂ ወይም አሳዳጊ (Guardian) አድርጎ መውሰድን የመሰሉ አድሎአዊ ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ ባለሥልጣኖች በቤተሰብ ላይ የሚደረግ ጥቃትን ለፍች የሚያበቃ ዋና ምክንያት አድርገው አልቆጠሩትም፡፡ ባህላዊ የጋብቻ ሕግ በፍትሕ ሥርዓቱ የተሰጠው እውቅና በተወሰነ ደረጃ ብቻ ነበር፡፡ ጋብቻው ጸንቶ የቆየባቸው ዓመታት ቁጥር፣ የልጆች ብዛትና የጋራ ሀብት ንብረቶች ከስሌት ሳይገቡ በባህላዊ የጋብቻ ሕግ ላይ የተመሠረተው ጋብቻ ሲያከትም፣ ሕጉ ሴቶችን ባለመብት የሚያደርጋቸው ለስድስት ወር የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነበር፡፡ ለቤተሰቡ የገንዘብ ዕርዳታ እንዲሰጥ ሕጉ ባልዮውን አላስገደደውም፡፡ በመሆኑም በዚህ ዓይነቱ ጋብቻ ችግር ሲፈጠር፣ ሴቶችና ልጆች አንዳንድ ጊዜ ችላ መባል ገጥሟቸዋል፡፡ ከጋብቻ በፊት በባለቤትነት ተይዞ የነበረ ንብረት፣ በፍች ጊዜ ይዞታ የነበረው ተጋቢ ይሆናል ሲል ሕጉ ያዛል፡፡ ሚስት የሞተ ባልን ንብረት ባትወርስም፣ በጋብቻ ዘመን የተገኘ ሀብት ንብረትን ሁለቱ እኩል እንደሚጋሩት ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በይፋ የታወጁ ጠንካራ ሕጎች እያሉም፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ፣ አብዛኞቹ ያገሪቱ የገጠር ኗሪዎች፣ በባህላዊው ሕግ መጠቀማቸውን ቀጥለዋል፡፡

መሬት በሙሉ የመንግሥት ነበር፡፡ ሴቶች፣ ከመንግሥት መሬት በሊዝ መያዝ ቢችሉም፣ መንግሥትም ሴቶች በመሬት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ግልጽ ፖሊሲ ቢኖረውም፣ የገጠር አካባቢዎች ፖሊሲውን እምብዛም ተግባራዊ አላደረጉትም፡፡ የኢትዮጵያ ሴት የሕግ ባለሞያዎች ማህበር (ኢሴሕባማ) እንደዘገበው ከሆነ፣ በጋብቻ አማካይነት ካልሆነ በስተቀር፣ ከሞላ ጐደል በሁሉም ክልል ሴቶች

መሬት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን፣ ባልዮው ሲሞት ሌሎች የቤተሰቡ አባላት የመሬት ይዞታውን ከሚስትዮዋ ይወስዱታል፡፡

በከተሞች፣ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ሥራ የማግኘት ዕድል ነበራቸው፤ በተገኙትም የሥራ ቦታዎች ለተመሳሳይ ሥራ ለወንዶችና ለሴቶች እኩል ክፍያ አልሰጡም፡፡

ልጆች

ለልጆች የተሻለ የጤና እንክብካቤ፣ መሠረታዊ ትምህርትና ጥበቃ ለማድረግ መንግሥት ያለው አቅም የተወሰነ ቢሆንም፣ በልጆች ማህበራዊ፣ የጤንነትና ሕጋዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ የመያዶችን ጥረቶች ደግፏል፡፡ በትምህርት ቤት የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት መካከል፣ 20 በመቶ የሚሆኑት ት/ቤት ባይሄዱም፣ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ትምህርት የግድና ለሁሉም ነው፡፡ በሕግ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከክፍያ ነፃ ነው፡፡ ያገሪቱን ወጣት ለማስተናገድ በተለይ በገጠር አካባቢዎች በቂ ት/ቤቶች ካለመኖራቸውም በላይ፣ የደንብ ልብሶችና የመማሪያ ቁሳቁሶች ወጪ ለአብዛኞቹ ቤተሰቦች የማይከፈል ነበር፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የዕድሜ ክልል ውስጥ ከነበሩት ወንድ ልጆች 74 ከመቶው፣ ከሴቶች ደግሞ 59 ከመቶው የሚሆኑት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፤

በአዲስ አበባ የሴቶች የትምህርት ሽፋን ትንሽ ከፍ ይላል፡፡ ትምህርት ከጀመሩት ውስጥ፣ 29 ከመቶ የሚሆኑት ሁለተኛ ክፍል ከመድረሳቸው በፊት እንደሚተውና፣ አንደኛ ክፍልን ከጀመሩት መካከል ደግሞ 22 ከመቶው ብቻ ስምንተኛ ክፍልን እንደጨረሱ የመንግሥት ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡

የልጆች መጠቃት ችግር ነበር፡፡ የወጣት አጥፊዎችንና ወጣት የወንጀል ተጠቂዎችን መብቶች ለማስከበር፣ የአንድ መያድ (NGO) አባላት በ10 የአዲስ አበባ ፖሊስ የልጆች ጥበቃ ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ ገብተው ሠርተዋል፡፡ የልጆች ጥቃትና ወጣት አጥፊነትን በተመለከተ ስላሉት የሕግ ሂደቶች ጥቂት የፖሊስ መኮንኖች ሥልጠና ወስደዋል፡፡

ከህብረተሰቡ ዕምነትና ልማድ ጋር በተያያዘ በወጣት ልጃገረዶች የሚፈጸም ጥቃት አንድ ችግር እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ አስከፊ ግርዛት (FGM) በአብዛኞቹ ሴት ልጆች ጐጂ ባህላዊ ልማዶች፣ እንጥል መቁረጥ፣ (Uvulectomy) የወተት ጥርስ ማስወለቅ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የጠለፋ ጋብቻ እና በምግብና በሥራ ልጆችን መቅጣትን ይጨምራሉ፡፡

በአገሪቱ ምሥራቅ አፋር ክልል፣ አዛውንቶች ወጣት ሴቶችን ማግባታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ነገር ግን እንደሚዲያ ዘገባዎች ከሆነ ከፍተኛ ጥያቄና ሂስ እያስነሳ ነበር፡፡ በየአካባቢያቸው ስላሉት ጐጂ ባህላዊ ልማዶችና ያላቻ ጋብቻ፣ ግንዛቤን ከፍ በማድረግ፣ የከምባታ ሴቶች ራስ-አገዝ ማዕከልና የትግራይ ሴቶች ማህበርን የመሰሉ የአገር ውስጥ መያዶች የሕብረተሰባቸውን አመለካከት በተመለከተ አዎንታዊ ተፅዕኖ አድርገዋል፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ የአማራና የትግራይ ክልሎች መንግሥታት፣ ካለዕድሜ ጋብቻ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች ለወጣት ሴቶች በቋሚነት የሚቀጥሉ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጀምረዋል፡፡

ያለዕድሜ የሚመጣ እርግዝና ብዙ ጊዜ በፅንሱ ምክንያት ለሚደርስ የሰገራና ሽንት ቧንቧዎች ብልሽትና (obstetric fistulae) እንዲሁም ለዘላቂ መካንነት (incontinence) ይዳርጋል፡፡ ለቧንቧዎች ብልሽት (fistulae) ሕክምና የሚገኘው በአንድ ሆስፒታል ብቻ፣ ማለትም በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል፣ ሲሆን ይህ ተቋም በዓመት ከአንድ ሺሕ በላይ የፊስቱላ ቀዶ ሕክምና ያደርጋል፡፡ ሆስፒታሉ እንደገመተው፣ ለእያንዳንዱ ለተከናወነ ስኬታማ ቀዶ ሕክምና፣ ሕክምናው ያስፈልጋቸው እና ያላገኙት በቁጥር 10 ሴቶች ነበሩ፡፡ የወላጅ እናቶች ሞት መጠን በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም በከፊል መንስኤዎቹ ለነፍሰ ጡር ሴቶች የተወሰኑ የምግብ ዓይነቶች በልማድ ውጉዝ መሆናቸው (food taboos)፣ ድህነት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ እና ከአስከፊ ባህላዊ ግርዛት (FGM) በተለይ ደግሞ የብልትን ከንፈር አሟጥጦ ከመቅፈፍ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የመውለድ ውስብስብ ችግሮች ናቸው፡፡

ዓለም አቀፍ መያዶች (NGOs) እንደሚሉት፣ የልጆች ሽርሙጥና በተለይ በከተሞች አካባቢ እያደገ የመጣ ችግር ነበር፡፡ በአንድ መያድ ዘገባ መሠረት፣ በወሲብ ንግድ (prostitution) ከሚበዘበዙት ውስጥ፣ 60 ከመቶው በ16 እና 25 ዓመት ዕድሜ ክልል ነበሩ፡፡ አቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሴት ልጆች፣ በሆቴል ሠራተኛነት፣ በመጠጥ ቤቶች አስተናጋጅነት፣ በመዝናኛ ከተሞችና በገጠር የጭነት መኪና መናኸሪያዎች በሴት አዳሪነት ይሠራሉ፡፡

በተንሰራፋ ድህነት የተነሳ ወደ ከተሞች ፍልሰት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ኤችአይቪ/ኤይድስና ሌሎች በግብረ ሥጋ ግነኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች እና ውሱን የትምህርትና የሥራ ዕድሎች የልጆችን በግብረሥጋ ግንኙነት መበዝበዝ አባብሰውታል፡፡ ወደ ሽርሙጥና ወይም የግብረሥጋ ብዝበዛ ለተገፉ ልጆች መጠለያ፣ እንክብካቤና ወደ የቤተሰቦቻቸው በመመለስ ልጆችን የሚረዳው የጐዳና ላይ ልጆች

መድረክ በኢትዮጵያን (Forum on Street Children-Ethiopia) ጨምሮ ጥቂት መያዶች ተጠቂ ልጆችን ረድተዋል፡፡

ልጆችን ከሕግ ውጭ የማስወጣት ወይም በልጆች መነገድን የሚመለከቱ ዘገባዎች አልፎ አልፎ ነበሩ፡፡ ይኸም በሕገወጥ የጉዲፈቻ መረቦች (adoption rings) ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ተወስደው ከዚያም የተለያዩ ሌሎች ዜግነቶች እንዳሏቸው ተደርገው ለጉዲፈቻ ስለተሰጡበት ሁኔታ የተደረጉ ዘገባዎችን ያካትታል (ክፍል 5 ማስተላለፍን ይመልከቱ)፡፡

ልጆችን አቅማቸውና ዕድሜያቸው የማይፈቅደውን ሥራ ማሠራት (child labor) ከፍተኛ ችግር መሆኑን ቀጥሏል (ክፍል 6.መ. ይመልከቱ)፡፡

መንግሥት ጠቅላላ የጐዳና ላይ ተዳዳሪ ልጆችን ቁጥር ከ150 እስከ 200 ሺሕ አድርጐ ገምቶታል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በግምት ከ50 እስከ 60 ሺሕ የሚሆኑት በአዲስ አበባ ይገኛሉ፡፡ እንደተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት ፈንድ (UNICEF) ግምት ግን እነዚህ አሀዞች 600 እና 100 ሺሕ ናቸው፡፡ በሕመምና የቤተሰብ ገቢያቸው መቀነስ የተነሳ ወላጆች ልጆቻቸውን መንከባከብ አለመቻላቸው ችግሩን አባብሰውታል ብሎ ዩኒሴፍ ያምናል፡፡

እነዚህ ልጆች ይለምናሉ፣ አንዳንድ ጊዜም በቡድን ሆነው፣ አለያም በኢመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ (informal sector) ይሠራሉ (ክፍል 6.መ.ን ይመልከቱ)፡፡ የመንግሥትና የግል ዕጓለ-ማውታን ተቋማት የነበሩትን የጐዳና ተዳዳሪ ልጆችን ለመቀበል አቅም አልነበራቸውም፤ እናም ትላልቆቹ ታናናሾቻቸውን ብዙ ጊዜ አጥቅተዋቸዋል፡፡ ከከፋ የአቅም ማጣት የተነሳ፣ ሆስፒታሎችና የዕጓለ-ማውታን ድርጅቶች የተጣሉ ሕፃናትን አንድም ቸላ ብለዋቸዋል አለያም አይተው እንዳላዩ አልፈዋቸዋል፡፡ በልመና ገንዘብ የማስገኘት ችሎታቸውን ለማጐልበት ሲሉ፣ ሕፃናትን "ያገሮች" ("Handlers") አንዳንድ ጊዜ የልጆችን አካል አጉድለዋል ወይም ዓይናቸውን አጥፍተዋል፡፡

ሰዎችን ማስተላለፍ (በሰዎች መነገድ)

ለግዳጅ ሥራና ለወሲብ ብዝበዛ ሲባል ለሚደረግ የወንዶች፣ የሴቶችና ልጆች ማስተላለፍ፣ ኢትዮጵያ አንድ ምንጭ አገር ነበረች፡፡ ከፈቃድ ውጭ ለሆነ የገረድነት ሥራ፣ ወጣት ኢትዮጵያውያት ወደ ጅቡቲ፣ መካከለኛው ምሥራቅ በተለይ ወደ ሊባኖስ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ ሳውዲ ዐረቢያ እና ባሕሬን

ተወስደዋል፡፡ አነስተኛ መቶኛ ቁጥር ያላቸው ለወሲብ ብዝበዛ በሊባኖስ በኩል ወደ አውሮፓ ተወስደዋል፡፡ ለጉልበት ሥራ፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወንዶች ወደ ሳውዲና ሌሎች የባህረ ሰላጤው አገሮች ተወስደዋል፡፡

የመንገድ ላይ ንግድ ለመሰለ የግዳጅ ሥራ፣ ለቤት ሠራተኛነት፣ ከእነዚህ ባነሰ ደግሞ ለገንዘብ ማግኛ የወሲብ ብዝበዛ፣ በአገር ውስጥ ልጆችም አዋቂዎቹም ከገጠር ወደ ከተማ ተወስደዋል፡፡ ድንበር ዘለል የሰዎች ማስተላለፍ በኢትዮጵያ በዓመት 20 እና 25 ሺ ተጠቂዎችን እንደሚያካትት መያዶች ገምተዋል፡፡

የሰዎች ሕገወጥ ማስተላለፍን (በሰዎች መነገድን) ለማስቀረት ዝቅተኛ የተባሉትን ቅድመ ሁኔታዎች እንኳ መንግሥት ባያሟላም፤ ይህንኑ ለማድረግ የማይናቁ ጥረቶች እያደረገ ነው፡፡ ሕጉ ለሴቶችና ልጆች ሕገወጥ ማስተላለፍ እስከ 20 ዓመት እስራትና 10 ሺ ብር (1,150 ዶላር) የሚደርስ ቅጣት ጥሏል፡፡ የተጠረጠሩ አስተላላፊዎች በ1996 የታሰሩ ቢሆንም፣ በዓመቱ መጨረሻ፣ በስኬታማነት የተጠናቀቁ የክስ ሂደቶች አልነበሩም፡፡ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ከአካባቢ ፖሊሶች ጋር በአንድነት የሰዎችን ሕገወጥ ማስተላለፍ ሲከታተል፣ የፍትሕ ሚኒስቴር በበኩሉ የመንግሥትን ሕግ አስከብሯል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት ዓለምአቀፍ ሕገወጥ የሰዎች ማስተላለፍ ምርመራዎችን አግዟል፡፡

ወንጀል አዘል የሆኑ የማስተላለፍ ገጽታዎችን በተመለከተ ለፖሊስ የሚሰጡ የሥልጠና ኘሮግራሞች በዓመቱ ውስጥ ቀጥለዋል፡፡ ሥልጠናውን የሚሰጡት ተቋማት፣ ጥፋተኛ ሠራተኞችን ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ለመከላከል ወይም ጣልቃ ለመግባት አቅማቸውና ሥልጠናቸው ውሱን ነበሩ፡፡

የሴትኛ አዳሪነት ቤቶች (House of Prostitution)፣ በዕድሜ 11 ዓመት ብቻ የሆኑ ልጃገረዶችን መልምለዋል፤ በኤችአይቪ/ኤድስና በሌሎች በግብረሥጋ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች ለሚመጣባቸው አደጋም አላሳወቋቸውም፡፡ በ1995 የተደረገ ዓለምአቀፍ የቤተሰብ ጤና ሪፖርት እንደተመለከተው፣ በጣም ለጋ የሆኑ ልጃገረዶች በግብረሥጋ ግንኙነት ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች ነፃ ናቸው ብለው ስለሚያምኑ፣ ደንበኞች በተለይ የሚፈልጉት እነሱኑ ነው፡፡

ዓለምአቀፍ የፍልሰት ድርጅት (International Organization for Migration-IOM) በ1996 ሕገወጥ የሰዎች ማስተላለፍ "በሚያስደነግጥ መጠን እየጨመረ ነው" ሲል ዘግቧል፡፡ በአገር ውስጥ ስለሚካሄድ የሴቶችና ልጆች ሕገወጥ ማስተላለፍ ላይ በአንድ የውጭ መንግሥት በ1995 ዓ.ም. ባደረገው ጥናት ችግሩ የተንሰራፋ እንደሆነ

አረጋግጧል፡፡ ለጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ከሰጡት በእጅጉ የበዙት እንዳረጋገጡት በመደበኛ ያልተደራጁትና ተራ ወንጀለኛ የሆኑ አስተላላፊዎች ሴቶችንና ልጆችን በውሸት የሥራ ተስፋ በማባባል ከገጠር ወደ አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ያስገቧቸዋል፡፡ ከ459 መልስ ሰጪዎች ውስጥ፣ 46 ከመቶው ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሲሆን፣ 49 ከመቶ ደግሞ ከስምንተኛ ክፍል በላይ ምንም ትምህርት የሌላቸው ነበሩ፡፡ አዲሶቹ አድራሻዎቻቸው እንደደረሱ፣ 54 ከመቶው በቤት ሠራተኛ ነት ሠርተዋል፤ ከገጠር ወደ ከተማ በአስተላላፊዎች የተዛወሩት ሴቶችና ልጆች በመጠጥ ቤቶች ሥራ በመሠማራታቸው፣ ሴት አዳሪ በመሆናቸው ወይም የመንገድ ላይ ለማኝ እየሆኑ በመሄዳቸው 54 ከመቶ የነበረው የቤት ሠራተኞች ቁጥር ወደ 9 ከመቶ ወርዷል፡፡

የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሰዎች ሕገወጥ የማስተላለፍ ተግባር ስለመሳተፋቸው፣ ስለማመቻቸታቸው ወይም ይሁንታ ስለመስጠታቸው የተዘገበ ነገር አልነበረም፡፡ ድርጊቱ ሕገወጥ ቢሆንም፣ እንደ አንድ የጋብቻ መንገድ ሴቶችንና ልጃገረዶችን መጥለፍ አሁንም በኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ክልሎች እንደተስፋፋ ቀጥሏል (ክፍል 5 ሴቶች ይመልከቱ)፡፡

የግል አካላት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሰዎች ለሥራ ወደ ውጭ አገር ልከዋል፡፡ በዚህም ሳቢያ ሕገወጥ ሰው አስተላላፊዎች ሴቶችን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በተለይ ወደ ሊባኖስ፣ ሳውዲ ዐረቢያ፣ ባሕሬን እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በቤት ወይም የፋብሪካ ሠራተኛነት ልከዋል፡፡ ብዙ ጊዜ እንደሚሆነው እነዚህ ሴቶች ወደተባሉት አገሮች የሚተላለፉት በጅቡቲ፣ የመንና ሶሪያ በኩል ነው፡፡ የሊባኖስ ምርመራና ማገቻ ማዕከል ኃላፊ፣ ቤይሩት ውስጥ 30 ሺሕ ኢትዮጵያውያት እየሠሩ እንደነበር በጥቅምት ወር አስታውቀዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል አብዛኞቹ በሕገወጥ መንገድ የተወሰዱ ነበሩ፡፡ መንግሥትም በበኩሉ ውጭ አገር ሥራ የሚፈልጉ ሰዎችን መመዝገብ ጀምሯል፡፡ ለሥራ በሕገወጥ መንገድ ወደውጭ ከሄዱት ሴቶች መካከል 50 ከመቶው በሕጋዊ መንገድ ወደ ትውልድ አገራቸው መመለስ አይችሉም ነበር፡፡

በሕገወጥ ዝውውር ምክንያት ተጠቅተው ወደ አገራቸው ለተመለሱት መንግሥት ያደረገላቸው ዕርዳታ ትንሽ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሴት የሕግ ባለሞያዎች ማህበር ለእነዚህ ተጠቂዎች በተወሰነ ደረጃ ሕግ ነክ ዕርዳታ አድርጐላቸዋል፡፡ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መፍለስ የሚያስከትላቸውን አደጋዎች በተመለከተ፣ የፌዴራል ፖሊስ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ከሚዲያው ጋር አብሮ በመሥራት የሕዝቡን ግንዛቤ የሚያጐለብቱ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ በሠራተኛ

በማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የልጆች፣ የወጣቶችና የቤተሰብ ጉዳዮች መምሪያ፣ የልጆችን በወሲብ መብዝበዝ ለመከላከል በተቋቋመው ብሔራዊ አቅጣጫ ቀያሽ ኮሚቴ ሊቀመንበር ነበር፡፡ ከዓለምአቀፍ የፍልሰት ድርጅት (ዓፍድ) ጋር የተደረገ ምክክርን ጨምሮ፣ በዓመቱ ውስጥ አንዳንድ የመንግሥት ጅማሮዎች ነበሩ፡፡ ውጭ አገር በቤት ሠራተኛነት ማገልገል ስለሚያመጣው አደጋ ዓፍድ (IOM) ለወጣት ሴቶች የሚታደል ብሮሹር በነሐሴ ወር አሳትሟል፡፡ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በቤት ሠራተኛነት ወደ ውጭ ለመሄድ የሚጠባበቁ ሴቶችን የሥራ ውል ማየቱን ከመቀጠሉም በላይ፣ አጥጋቢ ሆነው ያላገኛቸውን የሥራ ውሎች ውድቅ አድርጓል፡፡ አውሮፕላን ማረፊያ የተመደቡ የኢምግሬሽን ባለሥልጣኖችም እንዲሁ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ለመሄድ የቀረቡ የቤት ሠራተኞች የሥራ ውሎችን መርምረዋል፡፡ ያም ሆኖ፣ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ፈላሽ (migrant) ሠራተኞችን የሚልኩ አስቀጣሪ ድርጅቶችን በመቆጣጠር ረገድ፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስኬታማነት ውሱን ነበር፡፡ ጥቂት አስቀጣሪ ድርጅቶች ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ መሥራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ በቤይሩትና ዱባይ የሚገኙት ያገሪቱ የቆንስላ ቢሮዎች፣ በሕገወጥ ዝውውር ወደ ሊባኖስና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ የተወሰዱ ኢትዮጵያውያትን መርዳታቸውን ቀጥለዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች

ሕጉ የድኩማን (persons with disabilities) መብቶችን እኩል ማስተናገድን እያዘዘ እያለ፣ በተባሉት መብቶቻቸው እንዲጠቀሙ ለማድረግ መንግሥት አስፈላጊ የሆኑ አግባቦችን (mechanisms) አላዘጋጀም፡፡ ዝቅተኛ የአካል ጉዳተኞች ሥራ ማግኘትን በተመለከተ አድልዎ እንደተደረገባቸው አማረዋል፡፡ የአካል ጉዳተኞች ካለችግር ወደ ሕንፃዎች እንዲገቡ እና እንዲወጡ መንግሥት አላመቻቸም፡፡ ሌሎች አገልግሎቶችንም አላቀረበላቸውም፡፡ ሕጉ ለአካልና ለአእምሮ ጉዳተኞች ተሀድሶ ትኩረት ቢሰጥም፣ ለእነዚህ ተግባራት መንግሥት ግብአቶችን ያዋለው በጥቂቱ ነበር፡፡

የአገር ውስጥ መያዶች (NGOs) እንደሚሉት ከሆነ፣ ስድስት ሚሊዮን አካል ጉዳተኞች ነበሩ፡፡ በግምት 800 ሺሕ የአእምሮ በሽታ ጉዳተኞች መኖራቸው ቢታወቅም፣ በአገሪቱ የነበረው የአእምሮ በሽታ መታከሚያ ሆስፒታል አንድ ብቻ ሲሆን በመላ አገሪቱ የነበሩት የአእምሮ በሽታ ሐኪሞችም 10 ብቻ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች የመንከባከብ ኃላፊነት ያለበት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡

የተለያዩ አናሳ ማህበረሰቦች (National/Racial Ethnic Minorities)

በአገሪቱ ውስጥ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ሲኖሩ፤ ካገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ 40 ከመቶ ሆኖ ከሁሉም በቁጥር የሚበልጠው የኦሮሞ ብሔረሰብ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሌሎች ብሔረሰቦችም ባገሪቱ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሕይወት ላይ ተፅዕኖ ቢያደርጉም፣ በሰሜን ደጋማ ያገሪቱ ክፍል የሚኖሩት አማራዎችና ትግሬዎች የላቀ ሚና ነበራቸው፡፡ የፌዴራል ሥርዓቱ አገሪቱን የከፋፈለው ከሞላ ጐደል የብሔረሰቦችን መለያ ድንበሮች በመከተል ስለነበረ፤ የክልል ግዛቶች (regional states) ከዚህ በፊቱ በበለጠ የራሳቸውን ጉዳይ የመቆጣጠር ሥልጣን ነበራቸው፡፡ አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንደኛ ደረጃ በብሔረሰብ ላይ መመሥረታቸውን እንደያዙ ቆይተዋል፡፡

የመከላከያ ሠራዊቱ በብሔረሰቦች ስብጥር ድርጅትነቱ እንዳለ ቢሆንም፣ የከፍተኛ መኰንኖች ክፍል በትግሬ ብሔረሰብ አባላት ቁጥጥር ስር ነበር፡፡ በግንቦቱ ምርጫዎች ወቅትና እነሱን ተከትሎ በተከሰቱት ሰልፎች ጊዜ፣ ባለሥልጣኖች የጦር ኃይሎች አማራ አባላትን አያስተማምኑም ብለው በጠረጠሩባቸው እና ተቃዋሚዎች ጠንካራ በነበሩባቸው አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ለተልዕኮ ያሰማሩት የትግሬ ወይም የጋምቤላ ወታደሮች እንደነበሩ በብዛት ተዘግቧል፡፡

በክልሉ ውስጥ የበላይ ከሆነው ጐሣ ካልሆኑ የመንግሥት ሹማምንት የመምህራንን እና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞችን ቅጥር ስለማቋረጣቸው አንዳንድ ዘገባዎች ነበሩ፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ በተለይ በምዕራብ፣ በደቡብና በምሥራቅ ያገሪቱ ክፍሎች በብሔረሰቦች መካከል ግጭቶች መከሰታቸውን ቀጥለዋል፡፡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርና መንግሥት ብዙ ጊዜ ተዋግተዋል፡፡ እንዲሁም በጋምቤላ፣ በሱማሌና ደቡብ ክልሎች በብሔረሰቦች መካከል ግጭቶች ነበሩ፡፡

በየብሔረሰቦች መካከል የተደረጉ ግጭቶች በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ሞት ምክንያት ሆነዋል፡፡ የብሔረሰብ ግጭቶች በኦሮሚያ ክልል፣ በምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሱማሌዎችና በኦሮሞዎች መካከል፣ በቦረና ዞን ደግሞ በጋብራዎችና ጉጂዎች መካከል መከሰታቸውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ- EHRCO) ዘግቧል፡፡ የካቲት 15 የታጠቁ ኢትዮጵያውያን የሱማሌ ብሔረሰብ ቡድኖች፣ የኦሮሞዎች መንደሮችን በማጥቃት 18 ሰዎችን ሲገድሉ 31 አቁስለዋል፣ 103 ቤቶችን አቃጥለዋል፣ ከብቶች ዘርፈዋል፣ ንብረት አውድመዋል፡፡ በታህሣሥ 1996 ከተካሄደው ውሳኔ ሕዝብ (referendum) በኋላ፣ ጥቂት የማይባሉ መንደሮችን

ሁለቱ፣ ማለትም የኦሮሞና ሱማሌ ክልሎች በአስተዳደር መለዋወጣቸውን ተከትሎ፣ ለ760 ሰዎች መፈናቀል መንስዔ የሆነ የሱማሌዎች ኦሮሞዎችን ማዋከብና ማስፈራራት ነበረ፡፡

በኢሰመጉ (EHRCO) ዘገባ መሠረት፣ መጋቢት 24 (April 12)፣ የታጠቁ ሱማሌዎች በጉሎ ኦዳ ወረዳ በኩርኩር ቀበሌ ገበሬ ማህበር አንድ መንደር አጥቅተው 14 ሰዎች ገድለዋል፣ 10 አቁስለዋል፣ 1,358 ኦሮሞዎችን አፈናቅለዋል፡፡ መጋቢት 25 (April 3)፣ በጋብራዎችና ጉጂዎች መካከል በቦረና ዞን በያቤሎ ወረዳ በተካሄደ ግጭት 24 ሰዎች ተገድለዋል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት ጣልቃ መግባት ግጭቱ እንዳይባባስ ቢያደርግም፣ ሚያዝያ 21 ውጊያው አገርሽቶ 19 ግለሰቦች ተገድለዋል፣ 30 ሺ ሰዎች ተፈናቅለዋል፣ 1,378 ቤቶች ተቃጥለዋል፡፡ ሰኔ 20 (June 27)፣ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በዳባ ወረዳ ሚኤሶ ላይ የሱማሌና ኦሮሞ ብሔረሰቦች አባላት ተጋጭተው 16 ኦሮሞዎች ሲገደሉ 25 ቆስለዋል፣ ቁጥራቸው ያልታወቀ ሰዎች ተፈናቅለዋል፡፡

ሐምሌ 17 እና 19 በጅጅጋ ከተማ ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች በአራት ሆቴሎችና በአንድ መኖሪያ ቤት ባፈነዷቸው የእጅ ቦምቦች 5 ሰዎች ሲገደሉ 31 መቁሰላቸው ኢሰመጉ (EHRCO) ዘግቧል፡፡ ፖሊስ ተጠርጣሪ ያላቸውን በቁጥጥር ስር ያዋለ ሲሆን፣ በዓመቱ መጨረሻ ሁኔታው እየተመረመረ ነበር፡፡ ፍትሕ ዘለል (extrajudicial) ግድያዎችን ጨምሮ በደርግ ዘመነ መንግሥት (1966-1983) ስለተፈጸሙ ወንጀሎች በይፋ የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀል ክስ የቀረበባቸውን በአዲስ አበባ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መዳኘቱን እና ለፍርድ ማቅረቡን ቀጥሏል (ክፍል 1.ሠ. ይመልከቱ)፡፡

ጥቅምት 10 ያገር ውስጥ ጋዜጦች እንደዘገቡት፣ ተቃዋሚውን ፓርቲ ቅንጅትን በመደገፋቸው በአካባቢው ሹማምንት ድብደባ፣ እስራትና እንግልት የደረሰባቸው ሁለት ሺሕ የኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ወለጋ ዞን ጊዳ-ኪራሙ መንደር ገበሬዎች መኖሪያቸውን በመተው በአካባቢው ወደሚገኙ ከተሞች ተሰደዋል፡፡ የጊዳ-ኪራሙ ሕዝብ በአንደኛ ደረጃ አማራ ሲሆን፣ የአካባቢው ሹማምንት ደግሞ በአብዛኛው ኦሮሞዎች በመሆናቸው፤ በመንደሯ ቀደም ሲል በብሔረሰቦች መካከል ግጭቶች ታይተውባታል፡፡ የክልሉ መንግሥትን ጣልቃ መግባት ተከትሎ አብዛኞቹ ገበሬዎች ወደ መኖሪያዎቻቸው ተመልሰዋል፡፡

ሌሎች ሕብረተሰብአዊ ጥቃቶችና አድሎዎች

ግብረ-ሶዶም በእስራት የሚያስቀጣ ሕገወጥ ድርጊት ነው፡፡ ማስገደድን ወይም አቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆችን (ከ13 እስከ 16 ዓመት) የሚመለከቱና ጭካኔ የነበረባቸው

መሆናቸው የተደረሰባቸው የዚህ ዓይነት ድርጊቶች፣ ከሶስት ወር ባላነሰ ወይም ከአምስት ዓመት በላይ በሚደርስ እስራት ያስቀጣሉ፡፡ ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያሉበት የግብረሰዶም ወንጀል ከሆነ፣ ሕጉ ከ5 እስከ 25 ዓመት የእስራት ቅጣት ያዛል፡፡ በኤችአይቪ/ኤድስ ተጠቂዎች አንፃር በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለው ማግለል በዓመቱ ውስጥ ቀጥሏል፡፡

ክፍል 6 የሠራተኛ መብቶች

ሀ) የመደራጀት መብት

ለብዙሀኑ ሠራተኞች ሕጉ የሠራተኛ ማህበር የማቋቋምና አባል የመሆን መብትን ይፈቅዳል፣ መንግሥትም ይህንኑ በተግባር ፈቅዷል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕጉ መምህራንን፣ የመንግሥት ሠራተኞችን፣ ዳኞችን፣ አቃብያነ ሕግ እና የደህንነት ሠራተኞችን ለይቶ ከመደራጀት ይከለክላል፡፡

በዓመቱ ውስጥ በሠራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴዎች ላይ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ታይቷል፡፡ ዓለም አቀፍ ነፃ የሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (International Confederation of Free Trade Unions) እንዳስገነዘበው ብዙ የሠራተኛ ማህበር መሪዎች ከቦታቸው ተነስተዋል፣ ወይም ከአገር እንዲሰደዱ ተገደዋል፣ ሌሎች ደግሞ ለእስር ቤት ተዳርገዋል፡፡

የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚያስፈልገው አነስተኛ የሠራተኞች ቁጥር 20 ነበረ፡፡ ሁሉም ማህበራት መመዝገብ ቢኖርባቸውም፣ መንግሥት የማህበራት ምዝገባን የመሰረዝ መብቱን እንደያዘ ነበር፡፡ በዓመቱ ውስጥ መንግሥት በዚህ ሥልጣኑ ስለመጠቀሙ የተዘገበበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ሕጉ አንድ የሠራተኛ ድርጅት ግልጽ በሆነ አኳኋን የፖለቲካ ሥራ እንዳይሠራ ይደነግጋል፡፡ በግምት 300 ሺ የሚሆኑ ሠራተኞች የሠራተኛ ማህበራት አባል ነበሩ፡፡

ለነፃው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ETA) መንግሥት እውቅና የሰጠ ቢሆንም፣ ከወርሃዊ ደመወዛቸው 2 ብር (0.23 ዶላር) በመቁረጥ፣ የመንግሥት ት/ቤቶች መምህራን በሙሉ ሌላ በመንግሥት የተፈጠረና በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሚንቀሳቀሰውን በስምም እንዲሁ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ETA) ተብሎ የሚጠራውን ማህበር በገንዘብ እንዲደግፉት መምህራኑ በባለሥልጣኖች ተገደዋል፡፡

በ1995 መጨረሻ፣ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የመንግሥቱ የመምህራን ማህበር ሕጋዊ አቋምም ሆነ በነፃው መምህራን ማህበር ንብረት ላይ የይገባኛል መብት እንደሌለው ወስኖ፣ ባለሥልጣኖችም የነፃውን ማህበር ሀብት ንብረት እንዲመልሱና ቢሮዎቹንም እንደገና እንዲከፍቱ በይኗል። በመንግሥት ስር የሆነው ኢመማ (ETA)፣ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ ፍ/ቤቱም ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምረው ትዕዛዝ ሰጥቷል። ዓመቱ ሲገባደድ ያ ምርመራ እንደቀጠለ የነበረ ሲሆን፣ ከፍተኛው ፍ/ቤት ነፃውን ኢመማ በማወቅ የሰጠው ውሳኔ ተግባራዊ አልተደረገም ነበር።

ከፅንሱ ጀምሮ የዘለቀው፣ በመንግሥት አለሁ ባይነት የተደራጀው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ETU) ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር መሆን ዓመቱን ሙሉ ቀጥሏል።

በሠራተኛ ማህበራት አባላትና አደራጆች አንፃር በአሠሪዎች የሚደረግና መደራጀትን የሚፃረር አድሎአዊ አሠራርን ሕጉ ቢከለክልም፣ በትጋት የሚንቀሳቀሱ የማህበራት አባላትን አሠሪዎች አዘውትረው ከሥራ እንደሚያባርሯቸው ማህበራቱ አስታውቀዋል። በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ፍ/ቤቶች ባለው ወረፋ የተነሳ፣ ሕገወጥ ከሥራ መባረርን አስመልክቶ የሚነሱ ክሶችን ለመወሰን ዓመታት ወስዷል። የሠራተኛ መሪዎች እንደሚሉት በሠራተኛ ማህበር እንቅስቃሴአቸው ምክንያት ከሥራ በመባረራቸው ክስ የመሠረቱ ሠራተኞች፣ ከአራት ወይም አምስት ዓመት በኋላ አሁንም ጉዳያቸው በእጥልጥል (Pending) ላይ ነበር። በፀረ-ሠራተኛ ማህበር አድሎአዊ አሠራር ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ አሠሪዎች፣ ከሠራተኛ ማህበር ጋር በተያያዘ ከሥራ ያባረሯቸውን ሠራተኞች ወደ ቦታቸው እንዲመልሷቸው ተገደዋል። በአጠቃላይም በተግባር ፈጽመውታል።

ለ) የመደራጀትና በሕብረት የመደራደር መብት

ሕጉ በሕብረት የመደራደር መብትን ያስከብራል፤ በተግባርም ዜጐች በዚህ መብት በነፃነት እንዲጠቀሙ መንግሥት ፈቅዷል። የሠራተኛ ጉዳዮች አዋቂዎች የጋራ የሥራ የሕብረት ስምምነቶች 90 ከመቶ በማህበር የተደራጁ ሠራተኞችን እንደሚሸፍኑ ገምተዋል።

ደመወዝን በተመለከተ የሠራተኛ ተወካዮች በድርጅት ደረጃ ተደራድረዋል። የታወቁት ክፍለ ኢኮኖሚ የሠራተኛ ማህበራት፣ አግባብ ያላቸው ደንቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ጥረት አድርገዋል።

ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች በተለይ የሚዘጋጁበት (export processing) ዞኖች የሉም፡፡

ጥቅማቸውን ለማስከበር ሠራተኞች ሥራ የማቆም መብታቸውን ሕጉ ቢፈቅድም፣ ይህን ዓይነት አድማ ከማድረጋቸው በፊት ቢያንስ ከ130 ቀናት በፊት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠትን የመሰሉ የሥራ ማቆም አድማ ማካሄድን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎችንና መመሪያዎችን ይኸው ሕግ ይዟል፡፡ በዓመቱ ውስጥ፣ ድራጋዶስ (Dragados) የተባለውን አውሮፓዊ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ ኩባንያ የተመለከተ አንድ የሥራ ማቆም አድማ ነበረ፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በእንጥልጥል ላይ ሲሆን ሠራተኞቹ ግን ወደ ሥራቸው ተመልሰዋል፡፡ ሕጉ፣ ቅሬታ ያላቸው ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከመጥራታቸው በፊት ከአሠሪዎቻቸው ጋር ለመስማማት ጥረት እንዲያደርጉ ያስገድዳል፤ ለዚህም ሕጉ ረጅም የሆነ ልዩነቶችን የማስታረቅ ሂደት አካቷል፡፡ ይህም አንድ አሠሪ ወደ ድርጅቱ እንዳይገቡ ሠራተኞችን የማገድ መብቱንም ይመለከታል፡፡ አንድ የሥራ ማቆም አድማ ተግባራዊ ለመሆን ከሚመለከታቸው ሠራተኞች በብዙሀኑ መደገፍ አለበት፡፡

ያም ሆኖ፣ ሠራተኞች ከላይ ከተቀሱት አማራጮች በአንዱም ሳይጠቀሙ ሥራ የማቆም መብታቸው እንደተጠበቀ ነው፡፡ ይህን ሲያደርጉ ግን ቢያንስ ከ10 ቀናት በፊት ሌላውን አካልና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ማሳወቅ፣ ለመስማማት ጥረት ማድረግ፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ቦርድ የተያዘ ከሆነ ደግሞ ከ30 ቀናት በፊት ማስጠንቀቂያ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

ሕጉ አስፈላጊ የሆኑ ግልጋሎቶች ሠራተኞችን የሥራ ማቆም አድማ ከማድረግ ይከለክላል፡፡ ይህም የአየር ትራንስፖርትና የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ሠራተኞችን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሠራተኞችን፣ የቤንዚን ማደያ፣ የሆስፒታልና ፋርማሲ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የቴሌኮሚኒኬሽንና የከተማ ጽዳት ሠራተኞችን ይጨምራል፡፡ በ1995 የወጣው የሠራተኛ አዋጅ ማሻሻያ አስፈላጊ ግልጋሎቶች ትርጓሜን በማጥበብ ለባቡር ሠራተኞች፣ ለከተማ ውስጥ ትራንስፖርት አገልግሎቶች፣ ለባንኮችና ለፖስታ አገልግሎት ሠራተኞች ሥራ የማቆም አድማ መብት ሰጥቷል፡፡

ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት (ILO) የአሠሪና ሠራተኛ ክርክሮች ለወራት ወይም ለዓመታት እንደሚዘልቁ አስገንዝቧል፡፡

ሕጉ የሥራ ማቆም አድማ በሚያደረጉ ሠራተኞች ላይ የአፀፋ እርምጃ መወሰድን ይከለክላል፡፡ ነገር ግን እንደሠራተኛ መሪዎች አባባል፣ ብዙሀኑ ሠራተኞች መንግሥት ይህንን ጥበቃ በሥራ ላይ ያውለዋል ብለው አላመኑም፡፡ ከዚህም ሌላ፣ ባለው ከፍተኛ ሥራ አጥነትና የሠራተኛ ጉዳዮችን ለመስማት የፍትሕ አካላቱ በሚወስዱት ረጅም ጊዜ ሳቢያ፣ ጥቂት ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማም ሆነ በሌላ የሠራተኛ ጥቅምና መብት ተኮር እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ፈርተዋል፡፡

በሰኔ ወር መንግሥት የሠራተኛ ሕጉን ይበልጥ በማሻሻል፣ በፌደራል መንግሥት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚነሱ የሠራተኛ ቅሬታዎችን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጡ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኞች ግንኙነት ቦርዶች በክልሎች እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ ማሻሻያው ይህንኑ ተልዕኮ ለማሟላት እንደአስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ጊዚያዊ ተመሳሳይ ቦርዶች በክልሎች እንዲሠሩ ይፈቅዳል፡፡

ሐ) በኃይል ወይም አስገድዶ ማሠራትን መከልከል

በሕፃናት የሚከናወንን ጨምሮ፣ ሕጉ በኃይል ወይም አስገድዶ ማሠራትን ቢከለክልም፣ የዚህ ዓይነት ድርጊቶች ስለመፈጸማቸው ዘገባዎች ነበሩ (ክፍል 5 እና 6.መ. ይመልከቱ)፡፡

መ) የልጆችን መሥራት መከልከልና ለሥራ የሚያበቃው ሕጋዊ አነስተኛ ዕድሜ

ልጆችን ማሠራት የሚከለክሉ ሕጎች ነበሩ፡፡ ሆኖም፣ መንግሥት በውጤታማነት በተግባር አላዋላቸውም፡፡ በመሆኑም በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ልጆችን ማሠራት በአስከፊ ችግርነቱ ቀጥሏል፡፡ በሕጉ መሠረት፣ ምንዳ ወይም ደመወዝ ለሚያስከፍል ሥራ አነስተኛው ዕድሜ 14 ዓመት ነው፡፡ ይሄም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማጠናቀቅ ከተቀመጠው ዕድሜ ጋር ይጣጣማል፡፡ ሆኖም፣ ሥራ ለመያዝ የተደነገገው አነስተኛ የዕድሜ ቅድመ ሁኔታ በሚገባ ሥራ ላይ አልዋለም፡፡ አደገኛና የሌሊት ሥራን መከልከል ጨምሮ፣ በ14 እና 18 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ልጆችን የሚሸፍኑ ልዩ ድንጋጌዎች በሥራና ሠራተኛ ሕጉ ተካተዋል፡፡

በሕግ ዕድሜአቸው በ14 እና 18 መካከል የሆነ ልጆች በቀን ከ7 ሰዓት በላይ እንዳይሠሩ፣ ከምሽቱ 4 እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባሉት ሰዓታት ውስጥ እንዳይሠሩ፣ በበዓላትና ከመደበኛ የሥራ ሰዓቶች በላይ (overtime) እንዳይሠሩ ይከለክላል፡፡ መንግሥት ለአደጋ የሚያጋልጥ (hazardous) ሥራ የሚለው የፋብሪካ ወይም

የሚንቀሳቀሱ ክፍሎች ባሉት መሣሪያ መጠቀምን የሚጠይቅ ወይም ማንኛውም በልጆች ጤንነት ላይ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ሥራን ነው፡፡

ልጆችን የሚመለከቱትን የሠራተኛ ሕጎች በሥራ የማዋል ኃላፊነት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤ ነገር ግን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለተግባሩ አስፈላጊውን ዝግጅትና ቁጥጥር አላደረገም፡፡ መንግሥት እነዚህን ድንጋጌዎች በመደበኛው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ለማስከበር ትንሽ ጥረት ያደረገ ቢሆንም፣ ልጆችን ማሠራት በአገሪቱ ዙሪያ በተለይ በግብርና ቦታዎችና በኢመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ፣ የተንሰራፋ እንደሆነ የማህበራዊ ደህንነት ተቆርቋሪዎች (social welfare activists)፣ የሲቪክ ማህበራት አደራጆች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና አሠሪዎች ተስማምተውበታል፡፡ በከተሞች አካባቢ ልጆች የተለያዩ ሥራዎችን ያከናወናሉ፡፡ እነዚህም፡- ጫማ መጥረግን፣ ልብስ መስፋትን፣ የታክሲ ተሳፋሪዎችን ማስተናገድን፣ ዕቃ መሸከምን፣ የሎተሪ ትኬትና ሌሎች ጥቃቅን ነገሮች እያዞሩ መሸጥንና እንስሳት ማገድን ይጨምራሉ፡፡ በገጠር አካባቢዎች ደግሞ ልጆች በቤተሰብ ማሳዎች፣ በትላልቅ የንግድ እርሻዎችና በቤት ሠራተኛነት ያገለግላሉ፡፡

በዓለምአቀፉ የሠራተኛ ድርጅት (ILO) ድጋፍ ልጆችን ማሠራት በተመለከተ በ1993 በተደረገ ቅኝት፣ ከልጆች 40 ከመቶ የሚሆኑት ዕድሜአቸው 6 ዓመት ከመሆኑ በፊት መሥራት እንደጀመሩ ተደርሶበታል፡፡ እንዲሁም ዕድሜአቸው ከ5 እስከ 17 የሆነ ልጆች፣ በአማካይ በሳምንት 32.8 ሰዓት እንደሚሠሩ ቅኝቱ ጠቁሟል፡፡ ዕድሜአቸው ከ5 እስከ 9 ዓመት ከሆኑት ልጆች በግምት 13 ከመቶው በሳምንት ከ58 እስከ 74 ሰዓት ሠርተዋል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ውስጥ፣ ከሁለት ሶስተኛ እጅ በላይ የሚሆኑት ሠርተው ያገኙትን ገንዘብ ለወላጆቻቸው ወይም ለአሳዳጊዎቻቸው እንደሚሰጧቸው ተናግረዋል፡፡ በመጥፎ አዝመራ የተነሳ የቤተሰብ ገቢ መቀነስና ትምህርት ማቋረጥ፣ ለልጆች በሥራ መጠመድ መጨመር አስተዋፅኦ ያደረጉ ሁለቱ ዋና ምክንያቶች ነበሩ፡፡

የልጅ ሠራተኞች ብዙ ጊዜ እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ በ1991 የተደረገ ጥናት ሥራ ከማይሠሩት ጋር ሲነፃፀሩ፣ ሥራ የሠሩ ልጆች እጥፍ የአካልና የሥነ አዕምሮ ጥቃት (abuse)፣ አምስት እጥፍ የወሲብ ጥቃት፣ እና ስምንት እጥፍ ችላ መባል እንደሚደርስባቸው ደምድሟል፡፡ በጥናቱ በተጠየቁት ረገድ አስግድዶ መድፈር የተፈጸመባቸው በቤት ሠራተኛነት ባገለገሉት ላይ ብቻ ነበር፡፡ በመንግሥት ትርጓሜ በጣም አስከፊዎቹ የልጆች ሥራ ዓይነቶች ሽርሙጥናና በግድ ይዞ ማሠራት (bonded labor) ናቸው፡፡

በዓመቱ ውስጥ፣ ከኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ወደ ሌሎች ክልሎች በሕገወጥ መንገድ ተወስደው በግድ ወይም በመታገት መልክ ተይዘው በቤት ሠራተኛነት ይሠሩ የነበሩ ልጆች እንደነበሩ ተዘግቧል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)፡፡

ረ) ተቀባይነት ያላቸው የሥራ ሁኔታዎች

ለሥራ ብሔራዊ አነስተኛ ክፍያ የለም፡፡ ሆኖም፣ ጥቂት የመንግሥት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች የራሳቸውን አነስተኛ ከፍያ ወስነዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ከሁሉም ትልቁ የደመወዝተኞችን ክፍል የያዘው የመንግሥቱ ዘርፍ ተቀጣሪዎች አነስተኛውን የወር ደመወዝ ብር 200 (23 ዶላር) አግኝተዋል፡፡ በአንፃሩ የባንክና ኢንሹራንስ ዘርፍ ሠራተኞች አነስተኛ የወር ደመወዝ ብር 230 (27 ዶላር) ነበረ፡፡ የደመወዝና ሌሎች ክፍያዎች ጥናት ቢሮ እንደገለጠው፣ እነዚህ የደመወዝ ክፍያዎች ለአንድ ሠራተኛና ቤተሰቡን ተገቢ በሆነ የኑሮ ደረጃ መኖር የሚያስችሉ አልነበሩም፡፡ ይህም ስለሆነ፣ የደመወዝተኛው ክፍል የሆኑ አብዛኞቹ ቤተሰቦች በሕይወት ለመቆየት ቢያንስ ሁለት ደመወዝተኛ አባላት እንዲኖራቸው ግድ ነው፡፡ በመሆኑም ብዙ ልጆች ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ይገደዳሉ፡፡ ከጠቅላላው ሕዝብ ደመወዝ በሚያስከፍል ሥራ የተሠማራው በመቶኛ ሲወሰድ በጣም ትንሽ ነበረ፡፡ ይህም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ የተከማቸ ነበር፡፡

ሕጉ 24 ሰዓታት የእረፍት ጊዜ ያለው ባለ 48 ሰዓት የሥራ ሳምንት ያዛል፡፡ ከመደበኛው የሥራ ሰዓት በላይ ለሚሰጥ አገልግሎት (overtime) ተጨማሪ ክፍያ ሲያስገድድ፣ ከልክ ያለፈና የግዳጅ ተጨማሪ ሥራን ይከለክላል፡፡ ምንም እንኳ መንግሥት የሥራ ሕጉን ለማስከበር ብዙ ባያደርግም፣ በተግባር አብዛኞቹ የመደበኛው (formal) ክፍለ ኢኮኖሚ ተቀጣሪዎች በሳምንት 40 ሰዓታት ሠርተዋል፡፡

የሠራተኛ ጤንነትን ለማስጠበቅና የሥራ ላይ ደህንነት ደረጃዎችን ለመወሰን መንግሥት፣ ኢንዱስትሪና የሠራተኛ ማህበራት ተደራድረዋል፡፡ ሆኖም፣ በብቃት ማነስ የተነሳ፣ በሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሠራተኛ ጤንነት እና ደህንነት ቁጥጥር መምሪያ እነዚህ ደረጃዎች በሚገባ ሥራ ላይ እንዲውሉ አላደረገም፡፡ በተጨማሪም፣ ዝርዝር ዘርፍ ጠቅሶ የጤንነት እና ደህንነት መመሪያዎች አለመኖር የእነዚህን ደረጃዎች ማስከበር ከልክሏል፡፡ ሥራቸውን የማጣት ስጋት ሳይኖርባቸው ሠራተኞች አደገኛ ከሆኑ ሁኔታዎች ራሳቸውን የማግለል መብት ነበራቸው፡፡ ሆኖም፣ ይህን ቢያደርጉ ሥራቸውን እንደሚያጡ አብዛኞቹ ሠራተኞች ፍርሃት ነበራቸው፡፡